የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ

የአሠራር ስነ ሥርዓት ደንብ

ሰኔ **2016** ዓ.ም

አዲስ አበባ

መግቢያ..... 6

ክፍል አንድ ጠቅላላ ድንጋጌዎች.....6
አንቀጽ 1 - አጭር ርዕስ.....6
አንቀጽ 2 - ትርጉም.....6
አንቀጽ 3 - የተፈጻሚነት ወሰን.....8
ክፍል ሁለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ አባላት ነጻነትና የጉባዔው የአሠራር መርሆዎች.....9
አንቀጽ 5- ጉባዔው በሕገ መንግሥት ትርጉም ስለሚከተላቸው መርሆዎች.....9
አንቀጽ 6 - የጉባዔው አባላት ነጻነት፣.....9
አንቀጽ 7 - በጋራ ስለመሥራት.....9
አንቀጽ 8 - ግልጽነት.....9
አንቀጽ 9 - እኩልነት.....9
አንቀጽ 10 - ተፈጻሚ ስለሚሆኑ የሕገ መንግሥት ትርጉም መርሆዎች.....9
ክፍል ሦስት ከጉባዔ አባልነት ስለመሰናበት እና ከማጣራት ተግባር ስለመነሳት.....10
አንቀጽ 11 - በጉባዔው አባል ጥያቄ ስለመሰናበት.....10
አንቀጽ 12 - ከኃላፊነት ስለመሰናበት.....10
አንቀጽ 13 - የጉባዔ አባል ከኃላፊነት እንዲነሳ ጥያቄ የሚቀርብበት ሥርዓት.....11
አንቀጽ 15- ስለ ንዑስ አጣሪ ጉባዔ፣.....13
ክፍልአራት የጉባዔው ተግባር.....13
አንቀጽ 16 - የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የሥረ ነገር ሥልጣን፣.....13
አንቀጽ 17 - የጉባዔው ሰብሳቢ ተግባራት፣.....14
አንቀጽ 18 - የጉባዔው ምክትል ሰብሳቢ.....14
አንቀጽ 19 - የንዑስ አጣሪ ጉባዔ ተግባራት፣.....15
አንቀጽ 20 - የንዑስ አጣሪ ጉባዔ ሰብሳቢ ተግባራት፣.....16
አንቀጽ 21 - የንዑስ ጉባዔው ምክትል ሰብሳቢ ተግባራት፣.....16
አንቀጽ 22 - የጽሕፈት ቤቱ ተግባራት.....16
ክፍል አምስት.....18
የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ እና አቤቱታ አቀራረብ.....18
አንቀጽ 23 - የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ አቀራረብ፣.....18
አንቀጽ 24- በፍ/ቤት በተያዙ ጉዳዮች ላይ ስለሚቀርብ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ፣.....18
አንቀጽ 25- ከፍርድ ቤት ውጭ በሕግ ሕገ መንግሥታዊነት ላይ የሚቀርብ ጥያቄ፣.....19
አንቀጽ 26 - በፍርድ የማይወሰን ጉዳይ አቀራረብ.....19
አንቀጽ 27 - የሚመለከተውን አካል ስለመጋበዝ፣.....19
አንቀጽ 28 - የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄዎችን ወይም አቤቱታዎችን ስለማጣመር.....19
ክፍል ስድስት.....20

የአቤቱታ አቀራረብ፣ ይዘትና አባሪዎች.....20
አንቀጽ 29 - ስለ አቤቱታ አቀራረብ ፣.....20
አንቀጽ 30 -ስለአቤቱታው ይዘት፣
አንቀጽ 31- አባሪ ስለሚደረጉ ሰነዶች.....22
ክፍል ሰባት.....22
የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ ቅድመ ማጣራት እና ምርመራ.....22
አንቀጽ 32 - በሬጅስትራር የሚደረግ ማጣራት፣.....22
አንቀጽ 33 - በንዑስ ጉባዔ ስለሚደረግ ቅድመ ማጣራት፣.....22
አንቀጽ 34 - የትርጉም ጥያቄዎች ውድቅ ስለሚደረጉበት፣.....23
አንቀጽ 35 - የትርጉም አቤቱታ ወይም ጥያቄ ስለማቋረጥ፣.....23
ክፍል ስምንት.....24
መልስና የሙያ አስተያየት.....24
አንቀጽ 36 - ተጠሪ ስለሚያቀርበው መልስ፣.....24
አንቀጽ 37 - መጥሪያ ስለመላክ.....24
አንቀጽ 38 - ለጉባዔው ስለሚቀርብ የሙያ አስተያየት.....25
አንቀጽ 39 - አሚከስ ኩሪ ስለሚያቀርቡ አካላት፣.....26
አንቀጽ 40 - ለተቋማትና ባለሞያዎች የሚደረግ ግብዣ፣.....26
አንቀጽ 41 - የሙያ አስተያየት ይዘትና አቀራረብ.....27
ክፍል ዘጠኝ.....27
ክርክር ስለመስማት.....27
አንቀጽ 42 - ለክርክር ስለሚቀርቡ ጉዳዮች፣.....27
አንቀጽ 43 - የመስማት ሂደት ሳይኖር ስለመወሰን.....28
አንቀጽ 44 - የመስማት ሂደት ለማከናወን ዝግጅት ስለማድረግ፣.....28
አንቀጽ 45 - የመተባበር ግዴታ.....28
አንቀጽ 46 - መረጃዎችን ስለማሰራጨትና የመስማት ሂደት የሚካሄድበትን ስለማሳወቅ.....29
አንቀጽ 47 - በመስማት ሂደት ላይ ስለሚካፈሉ አካላት.....29
አንቀጽ 48 - የመስማት ሂደት በግልጽ መድረክ ስለማድረግ.....30
አንቀጽ 49 - የመስማት ሂደት በዝግ ስለማድረግ.....30
አንቀጽ 50 - የመስማት ሂደቱን ስለመክፈት.....30
አንቀጽ 51 - ቀጠሮ ስለመቀየር.....31
አንቀጽ 52 - የተከራካሪ ወገኖች የማጠቃለያ ሐሳብ.....31
አንቀጽ 53 - የመስማት ሂደቱን ስለማጠናቀቅ.....31

ክፍል አሥር....31
የጉባዔውና የንዑስ አጣሪ ጉባዔው ስብሰባና ውይይት....31
አንቀጽ 54 - ምልዓተ ጉባዔ....31
አንቀጽ 55 - የጉባዔው ውይይት....32
አንቀጽ 56 - ስለንዑስ አጣሪ ጉባዔ ስብሰባ....32
አንቀጽ 57 - የንዑስ አጣሪ ጉባዔው የውይይት ሂደት....33
ክፍል አሥራ አንድ....34
የጉባዔው ውሳኔ እና የውሳኔ ሐሳብ....34
አንቀጽ 58 - ውሳኔ እና የውሳኔ ሐሳብ ስለማሳለፍ....34
አንቀጽ 59- የልዩነት ሐሳብ....34
አንቀጽ 60 - ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሐሳብ መነሻዎች....35
አንቀጽ 61 - የውሳኔ እና የውሳኔ ሐሳብ ይዘት....35
አንቀጽ 62 - የውሳኔው ተፈጻሚ ክፍል፣....36
አንቀጽ 63- ውሳኔ ስለማስፈጸም....36
አንቀጽ 64 - ውሳኔ ስለማሳወቅ....37
አንቀጽ 65- የጉባዔውን ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሐሳብ ስለማረም....37
አንቀጽ 66 - ስለይግባኝ....37
አንቀጽ 67 - የውሳኔ ሐሳብ ስለመላክ፣....37
ክፍል አሥራ ሁለት....38
ልዩ ልዩ....38
አንቀጽ 68 - የዕግድ ጥያቄ አወሳሰን....38
አንቀጽ 69 - የጉዳዮችን ሚስጥራዊነት ስለመጠበቅ....39
አንቀጽ 70 - የጉዳዮች ፋይል አያያዝ....39
አንቀጽ 71 - የመወከል መብት....39
አንቀጽ 72 - ስለ ጉባዔው የሥራ ቋንቋ....39
አንቀጽ 73 - የጉባዔ አባላት፣ የጠበቆችና የተሳታፊዎች የአለባበስ ደንብ....40
አንቀጽ 74 - ከሚዲያዎች ጋር የሚደረግ ግንኙነት....40
አንቀጽ 75 - የመገናኛ ብዙኃን የመረጃ አጠቃቀም....40
አንቀጽ 76 - የመድረኩ ስነ ሥርዓት አከባበር....41
አንቀጽ 77 - ለሙያ አስተያየት አቅራቢዎች የሚፈፀም ክፍያ....41
አንቀጽ 78 - የመስማት ሂደት መረጃ አያያዝ....42
አንቀጽ 79 - ስለ ይርጋ....42
አንቀጽ 80 - ቃለ መሀላ....43

አንቀጽ 81 - የጉባዔ አባላት ሽኝት.....43
አንቀጽ 82 - መመሪያ የማውጣት ስለጣን.....43
አንቀጽ 83 - ስለሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት.....43
አንቀጽ 84 - የአሠራር ስነ ሥርዓቱን ስለማሻሻል.....44
አንቀጽ 85 - የአሠራር ስነ ሥርዓቱ ተፈጻሚነት.....44

መግቢያ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ተቋቁሞ፣ ሥልጣንና ተግባሩም በአንቀጽ 84 ስር ጠቅለል ባለ መልኩ የተደነገገ በመሆኑ፣

አጣሪ ጉባዔው የሕገ መንግሥት ጉዳዮችን የማጣራት ኃላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣትና የሥራ ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ የሚያስችለውን አሠራር ሊዘረጋ እንደሚችል በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገ በመሆኑ፣

አጣሪ ጉባዔው ለሚቀርቡለት የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄዎችና አቤቱታዎች ውሳኔ ለመስጠት ወይም የውሳኔ ሐሳብ ለማቅረብ የማጣራት ሥራውን በፍጥነት፣ በጥራት፣ በግልፅነት፣አገልግሎቱን ለተገልጋይ ምቹ ማድረግ የሚያስፈልግ በመሆኑ፣

የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔን ውጤታማነት ማሻሻል በማስፈለጉ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 84 ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት የሚመራበት ይህ የአሠራር ስነ ሥርዓት ደንብ ወጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 1 - አጭር ርዕስ

ይህ የአሠራር ስነ ሥርዓት "የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የአሠራር ስነ ሥርዓት ቁጥር .... *2016* ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

አንቀጽ 2- ትርጉም

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ የአሠራር ስነ ሥርዓት ውስጥ፦

2.1 "ሕገ መንግሥት " ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት ነው።

2.2 "ሕግ" ማለት በፌዴራል፣ በክልል ወይም በከተማ አስተዳደር ስር ባሉ የመንግሥት አካላት የወጡ አዋጆችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ይጨምራል።

2.3 "አዋጅ" ማለት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ አዋጅ ቁጥር 798/2005 ማለት ነው።

2.4 "የፌደሬሽን ምክር ቤት" ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 53 መሰረት የተቋቋመው ምክር ቤት ነው።

2.5 "ጉባዔ" ማለት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተቋቋመው የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ነው።

2.6 "ንዑስ አጣሪ ጉባዔ" ማለት ከሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ አባላት መካከል የሚመረጡ አባላትን የያዘ ጉባዔ ነው።

2.7 "ጽሕፈት ቤት" ማለት በአዋጅ ቁጥር 798/2005 አንቀጽ 27/1/ መሰረት የተቋቋመው የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ጽ/ቤት ነው።

2.8 “ክልል“ ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1) መሰረት የተቋቋመ ሲሆን በንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የተቋቋሙትንና ወደፊት የሚቋቋሙትንም ክልሎች የሚያካትት ነው።

2.9 “የከተማ አስተዳደር” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ናቸው።

2.10 “የመንግሥት አካል” ማለት የፌዴራል ፣ የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ሕግ አውጭ፣ ሕግ አስፈጻሚ እና የዳኝነት አካላትን ያጠቃልላል።

2.11 “ፍርድ ቤት” ማለት የፌዴራል፣ የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር በማናቸውም ደረጃ ያለ መደበኛ ፍርድ ቤት እና ሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን የተሰጠውን አካል ያጠቃልላል።

2.12 “የሕገ መንግሥት አቤቱታ” ማለት የአንድ የመንግሥት አካል ወይም የባለሥልጣን የመጨረሻ ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጠን መብት ወይም ነጻነት ጥሷል በሚል ለጉባዔው የሚቀርብ አቤቱታ ነው።

2.13 “የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ” ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (12) ከተመለከቱት የሕገ መንግሥት ትርጉም ጉዳዮች ውጭ ባሉ በማናቸውም ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች ላይ የሚቀርብ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ነው።

2.14 “የመጨረሻ ውሳኔ ”ማለት ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ወይም በሕግ የመዳኘት ሥልጣን በተሰጠው አካል፣ ወይም ለሌላ የመንግሥት አካል ቀርቦ የተወሰነና ሂደቱን ያጠናቀቀ ውሳኔ ነው።

2.15 “መስማት” ማለት የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ ወይም ጥያቄ አቅራቢ፣ መልስ ወይም አስተያየት ሰጪ እና ጉባዔውን በሙያ የሚያግዙ ወይም ተባባሪ የሚሆኑ ባለሙያዎች የሚያቀርቡትን ሐሳብና አስተያየት አጣሪ ጉባዔው እንደ አስፈላጊነቱ አስቀርቦ በቃል ማዳመጥ ነው።

2.16 “የጉባዔው አጋዥ (የአሚከስኩሪ አቅራቢ)” ማለት የክርክሩ ተካፋይ ሳይሆን በራስ ተነሳሽነት ወይም በጉባዔው ጠያቂነት ጉባዔውን በሙያ የሚያግዝ ወይም የሚተባበር ነው።

2.17 “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ነው።

አንቀጽ 3.የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ የአሠራር ስነ ሥርዓት ተፈጻሚነት የሚኖረው ለጉባዔው በቀረቡ በማናቸውም የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታዎችና ጥያቄዎች ላይ ነው።

አንቀጽ 4 - ስለ ጸታ አገላለጽ

በዚህ የአሠራር ስነ ሥርዓት በሌላ ሁኔታ እስካልተገለጸ ድረስ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው ድንጋጌ የሴትንም ጾታ ያካትታል።

ክፍል ሁለት

የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ አባላት ነጻነትና

የጉባዔው የአሠራር መርሆዎች

አንቀጽ 5- ጉባዔው በሕገ መንግሥት ትርጉም ስለሚከተላቸው መርሆዎች

5.1 **ጉባዔው የሕገ መንግሥት ትርጉም ሥራውን የሚያከናውነው በግልጽነትና በነጻነት ነው።**

5.2 ጉባዔው በበጀት፣ በአስተዳደራዊ ሥራዎች እና በሕገ መንግሥት ትርጉም ሥራው ሙሉ ነጻነት አለው።

አንቀጽ 6. የጉባዔው አባላት ነጻነት፣

6.1 የጉባዔው አባላት ሥልጣንና ተግባራቸውን በሕገ መንግሥቱ እና በዚህ የአሠራር ስነ ሥርዓት ደንብ መሰረት በሙሉ ነጻነትና በገለልተኝነት ያከናውናሉ።

6.2 አባላቱ የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፣ የዘር፣ የሃይማኖት፣ ወይም የመሳሰሉት ውግንና አይኖቸውም።

አንቀጽ 7. በጋራ ስለመሥራት

7.1 የጉባዔ አባላት ኃላፊነታቸውን የሚወጡት በመግባባት፣ በመከባበርና በመተባበር ነው።

7.2 ጉባዔው የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታዎችንና ጥያቄዎችን በማጣራት የሚወስነው ወይም የውሳኔ ሐሳብ የሚያቀርበው በተቻለ መጠን በተባበረ ድምጽ ይሆናል።

አንቀጽ 8.ግልጽነት

ለሕገ መንግሥት ትርጉም የሚቀርቡ እና በጉባዔው ውሳኔ የተሰጠባቸው፣ የውሳኔ ሐሳብ የቀረበባቸው እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው መረጃዎች ለሕዝብ ይፋ ይደረጋሉ።

አንቀጽ 9. እኩልነት

ጉባዔው የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታና ጥያቄ ያቀረቡ ወገኖችን እና ተጠሪዎችን በእኩልነት ያስተናግዳል።

አንቀጽ 10. ተፈጻሚ ስለሚሆኑ የሕገ መንግሥት ትርጉም መርሆዎች፣

10.1 ጉባዔው የሚቀርቡለትን የሰብአዊ መብት የሕገ መንግሥት ትርጉም ጉዳዮች መርምሮ ለመወሰን ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች እና አህጉራዊ የሰብአዊ መብት ሕግጋት አተረጓጐም መርሆዎችን ሥራ ላይ ያውላል።

10.2 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባዔው የሕገ መንግሥት ትርጉም መርሆዎችን ወደፊት በሚያወጣው መመሪያ ለይቶ ሥራ ላይ ሊያውል ይችላል።

ክፍል ሦስት

ከጉባዔ አባልነት ስለመሰናበት እና ከማጣራት ተግባር ስለመነሳት

አንቀጽ 11 - በጉባዔው አባል ጥያቄ ስለመሰናበት

11.1 የጉባዔው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ከኃላፊነት የሚነሱበት ሕገ መንግሥታዊ አግባብ እንደተጠበቀ ሆኖ በሀገራቱ ርዕሰ ብሔር የሚሾም ወይም ከፌዴሬሽን ምክር ቤት የተወከለ የጉባዔ አባል በራሱ ተነሳሽነት ከአባልነት ለመልቀቅ ከፈለገ ጥያቄውን በቀጥታ እንደቅደም ተከተላቸው ለሪፐብሊኩ ፕሬዝዳንትና ለፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባዔ ያቀርባል። ሲፈቀድም ከጉባዔ አባልነት ይሰናበታል።

11.2 የሪፐብሊኩ ፕሬዝዳንት ወይም የፌደሬሽን ምክር ቤት የጉባዔው ሥራ እንዳይስተጓጎልና ሌላ የጉባዔ አባል በምክር ቤቱ እስከሚሾም የጉባዔው አባል ፍቃደኝነት ተጠይቆ ለተወሰነ ጊዜ በሥራው ላይ እንዲቆይ ሊያደርጉ ይችላሉ።

አንቀጽ 12 - ከኃላፊነት ስለመሰናበት፣

አንድ የጉባዔ አባል ቀጥሎ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ከኃላፊነት ሊሰናበት ይችላል፦

12.1 ከባድ ወንጀል ሲፈጽምና ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ሲረጋገጥ፣

12.2 በማንኛውም የጤና እክል ምክንያት ኃላፊነቱን እና ተግባሩን ማከናወን ሲያቅተው፣

12.3 ለተከታታይ 3 ወራት በዚሁ ወይም በሌላ በማንኛውም ምክንያት በጉባዔው ሥራ ላይ መገኘት ካልቻለ፣

12.4 ከጉባዔው ኃላፊነትና ተግባር የሚጻረር ተግባር ላይ ከተሰማራ

አንቀጽ 13.የጉባዔአባልከኃላፊነትእንዲነሳጥያቄየሚቀርብበትሥርዓት

13.1 የጉባዔ አባል ከኃላፊነት እንዲነሳ በሾማቸው አካል ወይም ማንኛውም የጉባዔ አባል ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል።

13.2 ከኃላፊነት የያነሳ ጥያቄው የስንብቱን ምክንያት፣ ተገቢነት ያላቸው ፍሬ ነገሮችን የያዙ ሰነዶች፣ ከጥያቄው ጋር ተያይዘው በአቤቱታ አቅራቢው ተፈርሞ ለጉባዔ ሰብሳቢ ይቀርባል።

13.3 የጉባዔው ሰብሳቢ የስንብትጥያቄውን ለጉባዔው ያቀርባል። በጉዳዩ ላይ የሚደረገውውይይት በሚስጥር መያዝ ይኖርበታል፣

13.4 የጉባዔው ሰብሳቢ እንዲሰናበት ለተጠየቀው የጉባዔ አባል እንዲሰናበት የተጠየቀበትን ምክንያት በጽሑፍ ያሳውቃልኔ እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮች የያዘ ማስረጃ አባሪ በማድረግ ጥያቄ ለቀረበበት የጉባዔው አባል እንዲደርስ ያደርጋል፣

13.5 ጉባዔው በቀረበው የስንብት ጥያቄ ላይ ይመክራል፣

13.6 ስንብት የተጠየቀበት የጉባዔ አባል ለጉባዔው ማብራሪያ ወይም ከጉባዔው አባላት ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲሰጥ ይደረጋል።

13.7 ጉባዔው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ስንብት የተጠየቀበት የጉባዔው አባል የማይገኝበት ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፣

13.8 የጉባዔው አባል እንዲሰናበት የሚጠይቀው አቤቱታ በስብሰባው በተገኙ የጉባዔ አባላት በአብላጫ ድምጽ የውሳኔ ሀሳቡን የጉባዔ አባሉን ለሾሙት ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፕሬዝደንት ወይም ለፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባዔ ለመጨረሻ ውሳኔ ያቀርባል።

14. ከጉባዔውየማጣራት ተግባር ስለመነሳት፣

14.1 አንድ የጉባዔ አባል ከዚህ ቀጥሎ ከተመለከቱት ምክንያቶች በአንዱ ከሕገ መንግስታዊ የትርጉም ጉዳዮች ማጣራት ሊነሳ ይችላል፥-

ሀ) ከባለጉዳዮቹ ከአንደኛው ወገን፣ ከጠበቃው ወይም ከወኪሉ ጋር የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው እንደሆነ፣

ለ) ከባለጉዳዮቹ የአንደኛው ወገን ሞግዚት፣ ነገረ ፈጅ ወይም ጠበቃ በሆነበት ጉዳይ ላይ የተነሳ አቤቱታ ወይም ጥያቄ የሆነ እንደሆነ፣

ሐ) አቤቱታ ወይም ጥያቄ የተነሳበትን ጉዳይ አስቀድሞ በዳኝነት ወይም በዕርቅ መንገድ ያየው ወይም የሚያውቀው እንደሆነ፣

መ) ከባለጉዳዮቹ ከአንደኛው ወይም ከጠበቃው ጋር በፍርድ ቤት የተያዘ ክርክር ወይም ሙግት ያለው እንደሆነ፣

ሠ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከተመለከቱት ምክንያቶች ውጭ ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት የማያስችል ሌላ በቂ ምክንያት ያለው እንደሆነ፣

14.2 አንድ የጉባዔ አባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 14.1 መሰረት የተቀመጡ ሁኔታዎች መኖራቸውን ሲያውቅ ጉዳዩን ከማየት እንዲነሳ ጉባዔውን መጠየቅ አለበት።

14.3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 14.2 በቀረበለት ጥያቄ መሰረት ጉባዔው በሕገ መንግሥቱ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት እና የአቤቱታውን ይዘት ከግምት ውስጥ በማስገባት አባሉ እንዲነሳ ሊወስን ይችላል። የቀረበው ጥያቄ በንዑስ አጣሪ ጉባዔ አባል ሲሆን ውሳኔው የሚሰጠው በንዑስ አጣሪ ጉባዔው ነው።

14.4 አንድ የጉባዔ አባል ገለልተኛ አይደለም የሚል አቤቱታ በባለጉዳይ የቀረበበት ሲሆን ጉባዔው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 14.1 የተጠቀሱት ሁኔታዎች መኖራቸውን በማረጋገጥ የጉባዔውን አባል በዚያ ጉዳይ የማጣራት ሥራ ውስጥ እንዳይሳተፍ ሊያደርግ ይችላል።

14.5 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 14.4 በባለጉዳይ የሚቀርበው ማመልከቻ ማጣራቱ ከመጀመሩ በፊት ወይም ማመልከቻ ለማቅረብ ምክንያት መኖሩን አመልካቹ እንዳወቀ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት።

አንቀጽ 15- ስለ ንዑስ አጣሪ ጉባዔ፣

15.1 ጉባዔው የሥራ ቅልጥፍናውን ለማረጋገጥ እንዲያመቸው የንዑስ አጣሪ ጉባዔዎች ይኖሩታል።

15.2 አንድ ንዑስ አጣሪ ጉባዔ ቢያንስ ሦስት አባላት ይኖሩታል።

15.3 የንዑስ አጣሪ ጉባዔ አባላት በጉባዔው የሚሰየሙ ይሆናል።

15.4 ንዑስ አጣሪ ጉባዔ ከአባላቱ መካከል የንዑስ አጣሪ ጉባዔ ሰብሳቢ ይመርጣል።

15.5 ጉባዔው የንዑስ አጣሪ ጉባዔ አባላት በሚጓደሉበት ጊዜ ከሌሎች የጉባዔ አባላት በመተካት እንዲሟላ ያደርጋል።

ክፍል አራት

የጉባዔው ተግባር

አንቀጽ 16– የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የሰረ ነገር ሥልጣን፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 84 የተደነገገው ጠቅላላ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አጣሪ ጉባዔው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የሰረ ነገር ሥልጣኖች ይኖሩታል፡-

16.1 በሕገ መንግሥቱ ለፌዴራል መንግሥት እና ለክልሎች ወይም ለሌሎች ተቋማት በተሰጡ የሥልጣን ወሰን ላይ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ሲነሳ፣

16.2 በማንኛውም የመንግሥት አካል ወይም የባለሥልጣን የመጨረሻ ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ የተደነገጉት መሰረታዊ መብቶቼና ነጻነቶቼ ተጥሰዋል በሚል ጥያቄ ለማቅረብ መብት ባለው ሰው አቤቱታ ሲቀርብ፣

16.3 በፌዴራል የመንግሥት አካላት መካከል ወይም በክልሎች መካከል የሚነሱ የሥልጣን ክፍፍል የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ሲቀርብ ፣

16.4 በፌዴራል የመንግሥት አካላት መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች ሲቀርቡ፣

16.5 በክልሎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን በተመለከተ ጥያቄ ሲቀርብ፣

16.6 በፌዴራል መንግሥቱ እና በክልል መንግሥታት መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች ሲኖሩ፣

16.7 በፍርድ ሊወሰን በማይችል በማናቸውም ሕገ መንግሥታዊ ጉዳይ ላይ በፌዴራል ወይም በክልል ሕግ አውጭ ምክር ቤት አንድ ሦስተኛ አባላት ወይም በፌዴራልም ሆነ በክልል አስፈጻሚ አካላት ጥያቄ ሲቀርብ፣

16.8 የፌዴራል መንግሥት የሚያወጣቸው ሕጎች በክልሎች ስለሚፈጸሙበት ሁኔታ አለመግባባት ሲፈጠርና ጥያቄውም በሚመለከተው አካል ሲቀርብ፣

16.9 ኢትዮጵያ ተቀብላ ያጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ከሕገ መንግሥቱ ጋር ይጋጫሉ የሚል አቤቱታ ሲቀርብለት የማጣራት፣

16.10 በከተማ መስተዳድሮች እና በክልሎች ወይም በፌዴራል መንግሥት መካከል የሚነሳን የሥልጣን ክርክር በተመለከተ ጉዳዩ ሲቀርብለት የማጣራት፣

16.11 የክልል ሕጎች ወይም የመንግሥት አካላት ውሳኔዎች የፌዴራሉን ሕገ መንግሥት ይጥሳሉ ተብሎ የትርጉም ጥያቄ ወይም አቤቱታ ለጉባዔው ሊቀርብ ይችላል።

16.12 ሌሎች መሰል የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄዎችንና አቤቱታዎችን ይጨምራል።

አንቀጽ 17 - የጉባዔው ሰብሳቢ ተግባራት፣

የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ሰብሳቢ፦

17.1 የጉባዔውን አጀንዳ በመቅረጽ ስብሰባዎችንና ውይይቶችን ይመራል፣ ይከታተላል።

17.2 የጉባዔውን እና የንዑስ አጣሪ ጉባዔውን የሥራ ሁኔታና አፈጻጸም እንዲሁም የስብሰባ አከባበር ስርዓት ይከታተላል፣ ያረጋግጣል።

17.3 ጉባዔው የሚያስተላልፋቸው ውሳኔዎች እና ትዕዛዞች መፈጸማቸውን ይከታተላል።

17.4 የጉባዔውን፣ የንዑስ አጣሪ ጉባዔውን፣ የጽ/ቤቱን እና በጉባዔው የተቋቋሙ ጊዜያዊ ጉባዔዎችንና ኮሚቴዎችን ሥራ በበላይነት ይከታተላል፣ ይመራል።

17.5 የእግድ ትዕዛዝ ይሰጣል፣ የተሰጠውን እግድ እንዲነሳ ያደርጋል።

17.6 ከላይ የተዘረዘረው እንደተጠበቀ ሆኖ ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልገው ተጨማሪ ሥልጣን በጉባዔው ሲሰጠው ይፈፅማል።

አንቀጽ 18 - የጉባዔው ምክትል ሰብሳቢ

18.1 የጉባዔው ሰብሳቢ በሌለ ጊዜ የጉባዔውን ሰብሳቢ ተክቶ ይሠራል።

18.2 በጉባዔው ሰብሳቢ ወይም በጉባዔው ተለይተው የተሰጡትን ዝርዝር ተግባራት ያከናውናል።

አንቀጽ 19- የንዑስ አጣሪ ጉባዔ ተግባራት፣

19.1 የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታዎችንና ጥያቄዎችን ቅድመ ምርመራ በማድረግ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልጋቸውን፣ የማያስፈልጋቸውን እንዲሁም አከራካሪ የሆኑ ጉዳዮችን ለይቶ ለጉባዔ ያቀርባል፣

19.2 ለጉባዔ የሚቀርቡ ጉዳዮች ለውሳኔ የሚረዱ ጭብጦችን፣ አግባብነት ያላቸው ሕጎችን ውሳኔዎችንና አስፈላጊ ሲሆን አግባብነት ያላቸው ተሞክሮዎችን በሚያሳይ መልኩ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ያደርጋል።

19.3 አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ባለጉዳዮችን፣ አግባብነት አላቸው ብሎ የሚያምንባቸውን ተቋማት ወይም ባለሙያዎችን አስቀርቦ ይሰማል።

19.4 ጉዳዮችን ለማጣራት አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነበትን ማንኛውንም ዓይነት ማስረጃ አስቀርቦ ይመረምራል።

19.5 በጽ/ቤቱ ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ጥናቶችና የሙያ አስተያየቶች ላይ ውይይት ያደርጋል፣ ግብዓት ይሰጣል፣ አስፈላጊ ሲሆንም ተጨማሪ ጥናት እንዲደረግ ሊያዝዝ ይችላል።

19.6 ጉዳዮችን ከተመደቡለት የጽ/ቤቱ የጥናትና ምርምር ባለሙያዎች ጋር በመሆን ያጣራል፤ እንደአስፈላጊነቱም በአካል የመስክ ጉብኝት በማድረግ የማጣራት ሥራውን ይከውናል።

19.7 ጥናት እንዲደረግባቸው በንዑስ አጣሪ ጉባዔው የተለዩ ጉዳዮች እንዲጠኑ ለጽ/ቤቱ አቅጣጫ ይሰጣል፣ ተግባራዊነታቸውንም ክትትል ያደርጋል።

19.8 ዕግድ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች በመለየት ለጉባዔው ሰበሳቢ ያቀርባል፣ ሰብሳቢው ሲያምንበት ዕግድ ይሰጣል። የተሰጠው ዕግድ በጉባዔው ውይይት ከተደረገበት በኋላ አሳማኝ ካልሆነ ዕግዱ ሊነሳ ይችላል።

19.9 ለጉባዔው አሠራር ውጤታማነት የሚረዱ አሠራሮችን ከጽሕፈት ቤቱ ጋር በመነጋገርና በመለየት ለጉባዔው ያቀርባል፣

19.10 ሌሎች በጉባዔው ተለይተው የሚሰጡትን ሥራዎች ያከናውናል።

አንቀጽ 20 - የንዑስ አጣሪ ጉባዔ ሰብሳቢ ተግባራት፣

20.1 የንዑስ አጣሪ ጉባዔው ሰብሳቢ ከጽ/ቤቱ ጋር በመነጋገር የውይይት አጀንዳ ያዘጋጃል፣ እንደአስፈላጊነቱ ከስብሰባው በፊት ለአባላቱ እንዲሰራጭ ያደርጋል፣ የንዑስ ጉባዔውን ስብሰባ ይመራል።

20.2 የንዑስ አጣሪ ጉባዔውን ስብሰባ ይጠራል፣ ስብሰባውን ይመራል፣

20.3 በጉባዔው የተሰጡ ውሳኔዎችና ትዕዛዞች እንዲሁም በንዑስ ጉባዔው የተሰጡ ትዕዛዞች መፈጸማቸውን ይከታተላል፣

20.4 መዝገቦች በቅደም ተከተል መቅረባቸውን ያረጋግጣል፣

20.5 ቅድሚያ እንዲሰጣቸው የተወሰኑ ጉዳዮችን እና በጉባዔው የታገዱ ጉዳዮችን ቅድሚያ ቀርበው እንዲጣሩ ያደርጋል፣

20.6 ንዑስ ጉባዔ ሥራዎቹን በብቃት እንዲፈጽም የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

20.7 ሌሎች በንዑስ ጉባዔው ተለይተው የሚሰጡትን ሥራዎች ያከናውናል።

አንቀጽ 21 - የንዑስ ጉባዔው ምክትል ሰብሳቢ ተግባራት፣

21.1 የንዑስ ጉባዔው ሰብሳቢ በሌለ ጊዜ ተክቶ ይሠራል።

21.2 በንዑስ ጉባዔው ሰብሳቢ ወይም በንዑስ ጉባዔው ተለይተው የተሰጡትን ዝርዝር ተግባራት ያከናውናል።

አንቀጽ 22 - የጽሕፈት ቤቱ ተግባራት

22.1 የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ወይም አቤቱታ ለማቅረብ የሚመጡ ባለጉዳዮችን ተቀብሎ ያስተናግዳል፣

22.2 በባለጉዳይ የቀረበው የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ወይም አቤቱታ ተሟልቶ መቅረቡን ያረጋግጣል፤ ተሟልቶ ሲቀርብ ፋይል ቁጥር በመስጠት መዝገብ ይከፍታል። በዚህ አሠራር ስነ ሥርዓት አንቀጽ 29 እና 30 መሠረት ተሟልቶ ያልቀረበ ጥያቄ፣ አቤቱታ ወይም መልስ ተሟልቶ እንዲቀርብ በጽ/ቤቱ ሬጅስትራር በኩል ለባለጉዳዩ ያሳውቃል።

22.3 ከጉባዔው ሰብሳቢ በሚሰጠው የሥራ ውክልና መሰረት የተከፈቱ መዝገቦችን ለጽ/ቤቱ የሕግ ተመራማሪዎች ይመራል። ተመራማሪዎችም አስፈላጊውን ጥናትና ምርመር እንዲያደርጉ ያመቻቻል።

22.4 ጉባዔው ወይም ከንዑስ ጉባዔው በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የጽ/ቤቱ የሕገ መንግሥት ተመራማሪዎች ረቂቅ ውሳኔና የውሳኔ ሐሳብ እንዲዘጋጅ ያደርጋል።

22.5 አንድ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ወይም የውሳኔ ሐሳብ ለማቅረቡ በፊት የሚያስፈልጉ መረጃዎች እንዲሰበሰብ ያደርጋል። ጉባዔው ወይም ንዑስ አጣሪ ጉባዔው ለውሳኔ አሰጣጥ አስፈላጊ የሚሆኑ ተጨማሪ ማስረጃዎች እንዲቀርብለት ሲጠይቅ ያሰባስባል።

22.6 በጉባዔው ሰብሳቢ በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት የጉባዔው የውይይት አጀንዳዎች ይቀርጻል፣ ለጉባዔው አባላት እንዲደርሱ ያደርጋል፣ መድረሳቸውን ያረጋግጣል፣ የስብሰባ ጥሪ ያደርጋል።

22.7 የጉባዔውን ውሳኔ፣ የውሳኔ ሐሳብ፣ ትዕዛዝ፣ ወይም ሌሎች አቅጣጫዎች ለሚመለከታቸው አካላት ያደርሳል፣ መድረሳቸውን ያረጋግጣል፣

22.8 በጉባዔው ስብሰባ ላይ የተጠሩ አባላት ወይም ባለጉዳዮች የጉባዔውን ሥራ ቋንቋ የማያውቁ በሆነ ጊዜ የትርጉም አገልግሎት እንዲሰጥ ያደርጋል፣

22.9 በባለጉዳዮች ሲጠየቅ የውሳኔ ግልባጭ በጉባዔው ሬጅስትራር ጽ/ቤት በኩል ይሰጣል፣ የውሳኔ ሀሳቦችን እና ይግባኝ የተጠየቀባቸውን መዝገቦች ግልባጭ ለፌዴሬሽን ም/ቤት ይልካል፣

22.10 የሚከፈቱ መዝገቦችን፣ ውሳኔና የውሳኔ ሐሳብ የተሰጠባቸውን መዝገቦች በማደራጀት ይይዛል፣

22.11 የጉዳዮችን ወቅታዊ ፍሰት በመተንተን በየጊዜው ጉባዔው በቀጣይነት ሊወስደው ስለሚገባ የአሠራር አቅጣጫ ይጠቁማል፣

22.12 የሕግ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ባለጉዳዮች በመለየት ነፃ የሕግ ድጋፍ ከሚሰጡ ተቋማት ጋር በማገናኘት አገልግሎቱን እንዲያገኙ ያመቻቻል።

22.13 ለጉባዔው ሥራ ስኬታማነት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

ክፍልአምስት

የሕገመንግሥትትርጉምጥያቄእናአቤቱታአቀራረብ

አንቀጽ 23- የሕገመንግሥትትርጉምአቤቱታአቀራረብ፣

23.1 በፍርድ ቤቶች፣ በመንግሥት አካላት ወይም ባለስልጣናት የመጨረሻ ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ መብቴ ወይም ነጻነቴ ተጥሷል የሚል ማንኛውም ሰው የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ ለጉባዔው ማቅረብ ይችላል።

23.2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 23.1 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ተቋማት፣ የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ሌሎች ህጋዊ ተቋማት ወይም ድርጅቶች ነገሩ የሚመለከታቸው መሆናቸውን ማስረዳት ሳይጠበቅባቸው በራሳቸው አነሳሽነት ወይም በተጎጂዎች ጠያቂነት አቤቱታ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

አንቀጽ 24- በፍ/ቤት በተያዙ ጉዳዮች ላይ ስለሚቀርብ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ፣

24.1 በፍ/ቤት በተያዙ ጉዳዮች የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የተነሳ እንደሆነ ጥያቄው ጉዳዩን በያዘው ፍ/ቤት ወይም በባለጉዳዩ ለአጣሪ ጉባዔው ሊቀርብ ይችላል።

24.2 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 24.1 አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለጉዳዩ ጥያቄውን ለአጣሪ ጉባዔ ከማቅረቡ በፊት ጉዳዩን የያዘው ፍ/ቤት የሕገ ትርጉም ጥያቄውን ለአጣሪ ጉባዔው እንዲልክለት አቤቱታ ማቅረብ ይኖበታል። ሆኖም ጥያቄው የቀረበለት ፍ/ቤት ጥያቄውን ያልተቀበለው ወይም ተቀብሎ ተገቢውን ትዕዛዝ ካልሰጠበት ጥያቄ አቅራቢው ይህንኑ ከሚያረጋግጥ ማስረጃ ጋር በቀጥታ ለጉባዔው ሊያመለክት ይችላል።

24.3 ፍ/ቤት የሕገ መንግሥት የትርጉም ጥያቄ የሚልከው ጉዳዩን ለመወሰን የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልጋል ብሎ ሲያምንና ትርጉም የሚያስፈልግበትን እና ለውሳኔው ተፈጻሚነት/አግባብነት የሚኖረውን የሕገ ጭብጥለይቶ በማብራራት ነው።

24.4 ጉባዔው በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በእንጥልጥል እንዲያቆይ ሊያዝ ይችላል፣

አንቀጽ 25-ከፍርድቤትጭበሕግሕገመንግሥታዊነትላይየሚቀርብጥያቄ፣

25.1 በፌደራል መንግሥት፣ በክልል ወይም በከተማ አስተዳደር ህግ አውጭ አካላት የሚወጡ ህጎች ከህገ መንግሥቱ ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ ያለውናበጉዳዩ መብትና ጥቅም አለኝ የሚል አካል ለጉባዔው ጥያቄውን ሊያቀርብ ይችላል።

25.2 የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ተቋማት፣ የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶችና ሌሎች ህጋዊ ተቋማት ወይም ድርጅቶች ነገሩ የሚመለከታቸው መሆናቸውን ማስረዳት ሳይጠበቅባቸው በራሳቸው ተነሳሽነት ወይም በተጎጂዎች ጠያቂነት የግለሰቦች ወይም የማህበረሰብን መብትና ጥቅም ወክለው ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

አንቀጽ 26-በፍርድየማይወሰንጉዳይአቀራረብ

26.1 በዚህ የአሠራር ነ ርዓት አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 1፣ ከ 3 እስ 5 የተደነገጉትን የሕገ ትርጉምጥያቄ ማቅረብ የሚችሉት የፌዴራል፣ የክልልና የከተማ አስተዳደር ምክር ቤቶች፣ የአስፈጻሚ አካላት ወይም የመጨረሻው የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ይሆናሉ።

26.2 በፍርድ ሊወሰኑ የማይችሉ በማናቸውም ጉዳዮች ላይየሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄየሚቀርበው 1/3ኛ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ በፌዴራል ምክር ቤት አባላት፣ በክልል ምክር ቤት ወይም በከተማ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት፣ ወይምበፌዴራል፣ በክልል ወይም ከተማ አስተዳደር የሚመለከተው አስፈፃሚ አካል ነው።

አንቀጽ 27- የሚመለከተውን አካል ስለመጋበዝ፣

27.1 ጉባዔው ለውሳኔ አሰጣጥ ይረዳል ወይም አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን ማንኛውም በጉዳዩ ላይ መብትና ጥቅም ያለውን ሰው በአመልካችነት ወይም በተጠሪነት እንዲገባ ያደርጋል።

27.2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 27.1 መሰረት ወደ ጉዳዩ እንዲገባ ተጠይቆ ያልቀረበ ከሆነ የሚሰጠው ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሐሳብ ተፈፃሚ ይሆንበታል።

አንቀጽ 28 -የሕገመንግሥትትርጉም ጥያቄዎችንወይምአቤቱታዎችንስለማጣመር

28.1 አንድ የህገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ወይም አቤቱታ ብዙ አመልካቾችን የሚመለከት ሲሆንና ጉባዔውም የሚወስንበት የሕገ ጭብጥ ተመሳሳይ ሆኖ ሲያገኘው የአመልካቾችን አቤቱታ ወይም ጥያቄ በአንድነት አጣምሮ ለማየት ይችላል።

28.2 ጉባዔው ጉዳዮችን አጣምሮ ለማየት ሲወስን የሚመለከታቸው ባለጉዳዮች እንዲያውቁት ያደርጋል።

ክፍልስድስት

የአቤቱታአቀራረብ፣ ይዘትና አባሪዎች

አንቀጽ 29.ስለአቤቱታአቀራረብ፣

29.1 የሕገመንግሥት ትርጉም ጥያቄ ወይም አቤቱታ የሚቀርበው በፌዴራል መንግሥት የሥራ ቋንቋበጽሑፍ ይሆናል።

29.2 አቤቱታው በባለጉዳዩ ወይም በሕጋዊ ወኪሉ ሊቀርብ ይችላል።

29.3 ጉባዔው በክልሎች በሚከፍተው ቅርንጫፍ ወይም በሌሎች የመንግሥት አካላት አማካኝነት አቤቱታዎችን ሊቀበል ይችላል።

29.4 አመልካቹ የትርጉም አቤቱታውን ወይም ጥያቄውን ጉባዔው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በኤሌክትሮኒክ አግባብ እንዲያቀርብ ያደርጋል።

አንቀጽ 30. ስለአቤቱታው ይዘት፣

አቤቱታው ግልፅና የተጣሰውን ሕገ መንግታዊ መብት ወይም ሥልጣን የሚያሳይ ሆኖ ቀጥሎ የተዘረዘሩትንመያዝ አለበት፤-

30.1 በፍ/ቤትበመታየትላይየሚገኝጉዳይንአስመልክቶየሚቀርብየሕገመንግሥትትርጉምጥያቄ በፍርድ ቤቱ የቀረበ ከሆነ የፍ/ቤቱን ወይም የችሎቱን ስምና አድራሻ፣ የዳኛውን ወይም የዳኞቹን ስም፣ የተከራካሪዎቹን ስም፣ የመዝገብ ቁጥሩን፣ በፍ/ቤቱ የተያዘውን ጉዳይ ምንነት፣ ፍ/ቤቱ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል ያለበትን ምክንያት የጉባዔውን ሕገ መንግሥታዊ ኃላፊነት ባከበረ መንገድ መላክ አለበት።

30.2 ከባለጉዳዮቹ በአንዱ የቀረበ ከሆነ የፍ/ቤቱን ወይም የችሎቱን ስምና አድራሻ፣ የተከራካሪዎቹን ስምና አድራሻ፣ የመዝገብ ቁጥሩን፣ በፍ/ቤቱ የተያዘው ጉዳይ ምንነት በአጭሩ፣ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄው በፍርድ ቤቱ በኩል እንዲቀርብለት ጠይቆ ተቀባይነት ያላገኘ መሆኑን፣ ጥያቄው በፍርድ ቤቱ ውድቅ የሆነበትን ቀን እና የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልጋል ያለበትን ምክንያት ማቅረብ አለበት።

30.3 በመንግሥት አካላት፣ በግል ድርጅቶች ወይም ባለስልጣኖቻቸው የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ ሕገመንግሥታዊነትን አስመልክቶ የሚቀርብ አቤቱታ ከሆነ የአመልካችና ተጠሪ ስምና አድራሻ፣ አቤቱታ የቀረበበት ቀን፣የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልጋል ያለበትን ምክንያት፣ በየደረጃው የተሰጡ ውሳኔዎችን በቅደም ተከተል አባሪ ተደርጎ መቅረብ አለበት።

30.4 በፌዴራል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በክልል ወይም በከተማ አስተዳደር የወጣ ህግ ሕገ መንግስታዊነት ጥያቄ ላይ የቀረበ ከሆነ የሕገ መንግሥት ጥያቄ የቀረበበት ህግ አጭር ርዕስ፣ ህጉ የወጣበትን ቀን፣ የአመልካችን ስምና አድራሻ፣ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የቀረበበት ድንጋጌ፣ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልጋል የተባለበትን ምክንያትና ትርጉም የተጠየቀበት ሕግ አባሪ ተደርጎ መቅረብ አለበት።

30.5 በመንግሥት አካላት የሚቀርብ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ወይም አቤቱታ ከሆነ የአቅራቢውን የመንግሥት አካል ስም፣ ሕጋዊ ማሕተምና አድራሻ፣ የመንግሥት አካሉ የበላይ ኃላፊ ወይም ወኪል ስምና ኃላፊነት፣ በጉዳዩ ተጠሪ ካለ የተጠሪውን ስምና አድራሻ፣ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል የተባለበትን ምክንያት መያዝ አለበት።

30.6 አቤቱታውን ወይም ጥያቄውን ያቀረበው ሰው ጥያቄው ወይም አቤቱታው በእውነት የቀረበ ስለመሆኑና ጉዳዩ ከዚህ በፊት ለጉባዔው ያልቀረበ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አለበት፣

30.7 አቤቱታው ወይም ጥያቄው አስጸያፊና ለሕዝብ ሞራል ተቃራኒ የሆነ አገላለጽ ወይም አላስፈላጊ ዝርዝር ነገሮች ወይም ከጉዳዩ ጋር ተዛማጅነት የሌላቸው ነገሮች መያዝ የለበትም።

አንቀጽ 31- አባሪስለሚደረጉሰነዶች

31.1 አቤቱታ አቅራቢው ከአቤቱታው ጋር በየደረጃው የተሰጡ ውሳኔዎችንአባሪ በማድረግ ማያያዝ ይገባዋል።

31.2 ከሕገመንግሥት ትርጉም ጥያቄው ወይም አቤቱታው ጋር አባሪ ተደርገው የሚቀርቡ ሰነዶች በፌዴራል መንግሥት የሥራ ቋንቋ ተተርጉመው መቅረብ አለባቸው።

31.3 አቤቱታው በወኪል የሚቀርብ ከሆነ ህጋዊ የውክልና ማስረጃ ተያይዞ መቅረብ አለበት።

ክፍልሰባት

የሕገመንግሥትትርጉምአቤቱታቅድመማጣራትእናምርመራ

አንቀጽ 32 በሬጅስትራር የሚደረግ ማጣራት፣

32.1 ለጉባዔው የሚቀርብ የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ በሚከተሉት ምክንያቶች በጉባዔው ሬጅስትራር ተቀባይነት ያጣል፣

ሀ. የአቤቱታ አቀራረብ መስፈርት የማያሟላ ከሆነ፣

ለ. ጉባዔው ከዚህ በፊት ውሳኔ የሰጠበት ከሆነ፣

ሐ. ሂደቱን ጨርሶ ያልቀረበ ከሆነ፣

መ. የይርጋ ጊዜው ያለፈ ከሆነ፣

32.2 አቤቱታ አቅራቢው ከላይ በንዑስ አንቀጽ አንድ ያላሟላውን ነገር አሟልቶ ሲቀርብ አቤቱታው አንዲከፈትለት አንደገና ማቅረብ ይችላል።

32.3 የጉባዔው ፅ/ቤት ከላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች ያላሟላ ስለመሆኑ በፅሁፍ ለአቤቱታ አቅራቢው ማሳወቅ አለበት፤ ሆኖም አቤቱታ አቅራቢው ጉባዔው በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥበት መጠየቅ ይችላል።

አንቀጽ 33 -በንዑስ ጉባዔ ስለሚደረግቅድመ ማጣራት፣

33.1 ለሕገ መንግሥት ትርጉም የቀረቡለትን ጉዳዮች ተቀብሎ ይመረምራል፣ በምርመራው በተጨማሪነት መታየት ያለባቸው ጉዳዮች ካሉ ይለያል።

33.2 ጉዳዮችን ከተመደቡለት የጽ/ቤቱ ጥናትና ምርምር ባለሙያዎች ጋር በመሆን ያጣራል፤ እንደአስፈላጊነቱም በአካል የመስክ ጉብኝት በማድረግ የሚጣራት ሥራውን ያከውናል፣

33.3 በቅድመ ምርመራ ወቅት ትርጉም ያስፈልጋቸዋል በማለት ያመነባቸውን፣ትርጉም አያስፈልጋቸውም እና በአከራካሪነታቸው የለያቸውን ጉዳዮች ለጉባዔው ለውሳኔ ያስተላልፋል፣

33.4 ለጉባዔው በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ ለውሳኔ የሚረዱ ጭብጦችን፣ አግባብነት ያላቸው ህጎችን፣ ውሳኔዎችንና አስፈላጊ ሲሆን አግባብነት ያላቸው ተሞክሮዎችን በሚያሳይ መልኩ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ያደርጋል፣

33.5 ጥናት እንዲደረግባቸው በጉባዔው ወይም በንዑስ አጣሪ ጉባዔው የተለዩ ጉዳዮች እንዲጠኑ በጉባዔው ወይም በንዑስ አጣሪ ጉባዔው ለጽ/ቤቱ አቅጣጫ ይሰጣል፣ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል።

አንቀጽ 34.የትርጉምጥያቄዎችውድቅስለሚደረጉበት፣

ጉባዔው የሚቀርብለትን የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ መርምሮ በሚከተሉት ምክንያቶች ውድቅ ሊደርግ ይችላል፡-

ሀ. ከጉባዔው ሥልጣን ጭ ሲሆን፣

ለ. አቤቱታ አቅራቢው ጉዳዩን ለማቅረብ መብት ወይም ሥልጣን የሌለው ከሆነ፣

ሐ. የሕገ ትርጉም የሚያሻው ከሆነ።

አንቀጽ 35- የትርጉምአቤቱታወይምጥያቄስለማቋረጥ፣

35.1 ማንኛውም የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ወይም አቤቱታ ጉባዔው በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በሚከተሉት ምክንያቶች በጉባዔው ሊቋረጥ ይችላል፡-

ሀ) ለጉዳዩ መቅረብ ምክንያት የሆነው ሕግ፣ ውሳኔ ወይም ድርጊት ቀሪ ከሆነ፣ ከተለወጠ ወይም ከተሰተካከለ፣

ለ) አመልካች አቤቱታውን ወይም ጥያቄውን እንደተወ በጽሑፍ ከገለጸ፣ ወይም

ሐ) ሕጉ፣ ውሳኔው ወይም ድርጊቱን ለመለወጥ፣ ቀሪ ለማድረግ ወይም ለማስተካከል የሚመለከተው አካል ለጉባዔው ማረጋገጫ ከሰጠ።

35.2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) መሰረት ጉባዔው ምርመራውን ያቋረጠው ድርጊቱ በሚመለከተው አካል ጥያቄ አቅራቢነት የሆነ እንደሆነ ጉባዔው ጉዳዩን ማጣራቱን የሚያቋርጠው ጠያቂው ተቋም ማስተካከያ ለማድረግ ለሚያስችለው ጊዜ ብቻ ይሆናል። ስለሆነም ጠያቂው ተቋም በተሰጠው ጊዜ ማስተካከያ የማያደርግ ከሆነ ጉባዔው ጉዳዩን ማጣራቱን ካቆመበት ይቀጥላል።

35.3 ጉባዔው በንዑስ አንቀጽ 35.1 መሰረት ለጉዳዩ መቅረብ ምክንያት የሆነው ሕግ፣ ውሳኔ ወይም ድርጊት የሚመለከተው አካል ጠርቶ እንዲያስተካክል ሊጠይቀው ይቻላል።

35.4 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ንዑስ አጣሪ ጉባዔው ወይም ጉባዔው ተገቢ ነው ብሎ ካመነ አቤቱታው ወይም ጥያቄው እንዳይቋረጥ ወይም የተቋረጠው የማጣራት እና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱ እንዲቀጥል ሊወስን ይችላል።

35.5 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 35.1 ፊደል "ለ" መሰረት የተቋረጠ የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ ወይም ጥያቄ አሳማኝ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በድጋሚ ለጉባዔው ቀርቦ ሊታይ አይችልም።

ክፍልስምንት

መልስናየሙያአስተያየት

አንቀጽ 36.ተጠሪ ስለሚያቀርበው መልስ፣

36.1 ጉባዔው በአንድ ጉዳይ ላይ የሕገ መንግሥት ትርጉም ሊያስፈልገው ይችላል የሚል እምነት ካሳደረ የበለጠ ለማጣራት እንዲያግዘ የተጠሪን መልስ መቀበል አለበት።

36.2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 36.1 መሰረት መልስ እንዲሰጥ የተጋበዘ ሰው ወይም የመንግሥት አካል በተሰጠው ጊዜ ውስጥ መልስ ያላቀረበ ከሆነ ንዑስ አጣሪ ጉባዔ ወይም ጉባዔው በቀረበለት ሰነድ ላይ ተመስርቶ ተገቢውን የማጣራት ተግባር ያከናውናል።

አንቀጽ 37–መጥሪያስለመላክ

37.1 ተጠሪመልሱንይዞእንዲቀርብ ጉባዔው ሲወስን የጉባዔው ፅ/ቤት አግባብነት ባላቸው የመገናኛ ዘዴዎች መጥሪያው ለተጠሪ እንዲደርስ ያደርጋል።

37.2 ተጠሪመልሳቸውን እንዲያቀርቡ መጥሪያ የሚላክላቸው በንዑስ አጣሪ ጉባዔው ወይም እንደ አስፈላጊነቱ በዋናው ጉባዔ የፀደቀ መነሻ ቁጥጥር፣ የአመልካችአቤቱታ፣ የፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ወይም የአስተዳደር አካላትን ውሳኔ ወይም የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የቀረበበትን ሕግ ከመጥሪያው ጋር አባሪ በማድረግ ይሆናል።

37.3 ተጠሪ መጥሪያው እንደሁኔታው በጉባዔው ጽ/ቤት፣ በአመልካች ወይም በፖስታ ወይም በኢ-ሜል በጉባዔው ዌብሳይት፣ በፈስቡክ፣በጋዜጣ ወይም አድራሻው በሚገኝበት አካባቢ ባለ የአስተዳደር አካል በኩል እንዲደርሳቸው ይደረጋል።

37.4 መጥሪያ ለመስጠት ተጠሪን ማግኘት ካልተቻለ ወይም ተጠሪው መጥሪያውን ለመቀበል ፍቃደኛ ካልሆነ ጉባዔው በፅ/ቤቱ ማስታወቂያ ቦርድ እና ኦፊሴላዊ ውብሳይት ላይ ለ 15 ተከታታይ ቀናት ይለጥፋል፤ ጉባዔው እንደአስፈላጊነቱ በጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ ሊያደርግ ይችላል።

37.5 በንዑስ አንቀጽ 37.4 የተደነገገው ስነ ሥርዓት ሲፈጸም ለተጠሪው መጥሪያ እንደደርሰው ይቆጠራል። ተጠሪው በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ ጉባዔው ጉዳዩን በሌለበት ያጣራል።

37.6 የተጠሪ የፅሁፍ መልስ በጉባዔው በተለየ ጭብጥ ላይ የተመሰረተ፣ ግልፅና ቀጥተኛ መሆን አለበት።

37.7 ጉባዔው የያዘውን መነሻ ጭብጥ በሙሉ ወይም በከፊል መለወጥ ወይም አዲስ ጭብጥ መቀየር አለበት የሚል ከሆነ በምክንያት አስደግፎ ሊያቀርብ ይችላል።

አንቀጽ 38 - ለጉባዔውስለሚቀርብየሙያአስተያየት

38.1 ጉባዔውአመልካችና ተጠሪ ካቀረቡት ፅሁፍ በተጨማሪ የባለሙያ አስተያየት መስማት ያስፈልጋል ብሎ ሲያምን አግባብነት ካላቸው ተቋማት እና ባለሞያዎችየሙያ አስተያየት እንዲቀርቡለት ሊያደርግ ይችላል። የሚሰጧቸውን ሃሳቦች ጉባዔው እንደአግባብነታቸው ለውሳኔው ወይም ለውሳኔ ሃሳቡ በግብአትነት ሊጠቀምባቸው ይችላል።

38.2 ጉባዔው የሙያ አስተያየት እንዲቀርብ የሚያዘው ለውሳኔው ወይም የውሳኔ ሐሳብ ለማቅረብ የሙያ አስተያየት መሰብሰብ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን ነው።

አንቀጽ 39 - አሚከስኩሪ አስተያየትስለሚያቀርቡአካላት፣

39.1 ጉባዔው በመመርመር ላይ ባለ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጉዳይ ላይባለሙያዎች፣ ተቋማት ወይም ማህበራት በጉባዔው ጋባዥነትሃሳባቸውን እንዲሰጡ ሊያደርግ ይችላል።

39.2 ከላይ በንዑስ አንቀጽ 39.1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጉዳይ ላይ አጋዥ ሚና አለን ብለው የሚያምኑ ባለሙያዎች፣ ተቋማት ወይም ማህበራት በራስ ተነሳሽነት አስተያየት ለመስጠትለጉባዔው ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። ጉባዔውም የአስተያየት አቅራቢዎችን ገለልተኝነት በማረጋገጥ ሊፈቅድላቸው ይችላል።

39.3 ጉባዔው አሚከስ ኩሪ የሚመራበትን አግባብ በተመለከተ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

አንቀጽ 40 - ለተቋማትና ባሞያዎች የሚደረግ ግብዣ፣

40.1 ጉባዔው የሙያ አስተያየት እንዲያቀርቡየሚጋብዘው ሰው፤ ግለሰብ ወይም አካል ገለልተኛናእንደ ጉዳዩ አግባብነት በዘርፉ ላይ በቂ እውቀትና ልምድ ያላቸው፣ ታዋቂ የሆኑ ምሁራንና በጉዳዩ ዙሪያ እየሰሩ ያሉ ተቋማትን እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትን ነው።

40.2 የሙያ አስተያየታቸውን እንዲያቀርቡ ለተመረጡ አካላት የአመልካች አቤቱታ፣ የተጠሪ መልስ፣ በጉባዔ የተለየ መነሻ ጭብጥ ከግብዣ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ እንዲደርሳቸው ይደረጋል። ሆኖም ጉዳዩ የተጠሪን ምላሽ በማይኖርበት ጊዜ የተጠሪን መልስ ላያካትት ይችላል።

40.3 የሙያ አስተያየት አቅራቢዎቹ ግብዣው በጽ/ቤቱ በኩል በደብዳቤ፣ በፖስታ፣ በኢ-ሜል ወይም በሌሎች ተገቢነት ባላቸው የተግባቦት ዘዴዎች እንዲደርሳቸው ይደረጋል።

40.4 የሙያ አስተያየት አቅራቢዎችም ግብዣው በደረሳቸው በ 20 የሥራ ቀናት ውስጥ አስተያየታቸውን ማቅረብ አለባቸው። ሆኖም በአስተያየት አቅራቢ ጠያቂነት እንደጉዳዩ ክብደትና ውስብስብነት ጉባዔው ተጨማሪ አስተያየት የመስጫ ጊዜ ሊጨምር ይችላል።

አንቀጽ 41 - የሙያአስተያየትይዘትናአቀራረብ

41.1 ጉባዔው የሙያ አስተያየት አቅራቢዎች የሙያ አስተያየቶቻቸውን በቃል እንዲያቀርቡ ካልፈቀደላቸው በቀር የሙያ አስተያየት የሚቀርበው በጽሑፍ ይሆናል።

41.2 የሚቀርበው የሙያ አስተያየት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፦

ሀ. በተላከው መነሻ ፅሁፍ ወይም ጭብጥ ላይ የተመሰረተ፣

ለ. ግልፅ፣ ቀላል፣ ቀጥተኛ፣ትንታኔና ማጠቃለያ ያለው፣

ሐ. ሙያዊ ሚዛናዊነትንና ገለልተኝነትን የጠበቀ፣

መ. የግለሰቦችን ወይም የቡድን መብትን የማይነካ፣ የተቋማትን ወይም ሌሎች አይነት ድርጅቶችን ክብር፣ ዝናና መልካም ስም የማይነካ፣

ሠ. የጉባዔውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ምርመራ ሥራ ሊረዳ የሚችል ግልፅ አቋም ወይም ሐሳብ የሚያሳይ፣

41.3 በጉባዔው ከተላከላቸው መነሻ ጭብጥ በተጨማሪ የሙያ አስተያየታቸውን ማቅረብ ሲፈልጉ ይህንኑ ጠቅሰው አስተያየታቸውን ለጉዳዩ አግባብነት ባለው ጭብጥ ላይ ተመስርተው ማቅረብ ይችላሉ።

41.4 የፅሁፍ የሙያ አስተያየት የሚቀርበው በጉባዔው ጽ/ቤት በአካል በመገኘት፣ በፖስታ፣ በኢ-ሜይል ወይም በሌሎች ተገቢነት ባላቸው የተግባቦት ዘዴዎች ሊሆን ይችላል።

ክፍልዘጠኝ

ክርክርስለመስማት

አንቀጽ 42-ለክርክርስለሚቀርቡጉዳዮች፣

42.1 ጉባዔው በተመረጡ ጉዳዮች ላይ ከጽሑፍ ምላሽ በተጨማሪ የቃል ክርክር ሊሰማ ይችላል።

42.2 ጉባዔው ተጠሪን ወይም ወደ ጉዳዩ በሚጋብዘው ወገን የጽሑፍ ምላሽ ሳይሰማ የቃል ክርክር እንዲደረግ የሚወስነው የቀረበለትን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ባህሪ፣ የጉዳዩን ዓይነትና ውስብስብነት፣ ክብደትና አከራካሪነት፣ የህዝብ ጥቅም ያለበት መሆን እና ለሌሎች አስተማሪ ሊሆን ይችላል ብሎ ሲያምን ነው።

42.3 ጉባዔውበበቂ ምክንያት ቅድሚያ እንዲሰጥ ካላደረገ በስተቀር ጉዳዮች እንደቅደም ተከተላቸው ይሰማሉ።

አንቀጽ 43- የመስማት/የክርክርሂደትሳይኖርስለመወሰን፣

43.1 ጉባዔው አሳማኝ ሆኖ ሲያገኘው የመስማት ሂደት ሳይከተል የተጠሪን መልስ እና የሙያ አስተያየት፣ ወይም የተጠሪን መልስ ብቻ መሰረት በማድረግ ውሳኔ ሊሰጥ ወይም የውሳኔ ሐሳብ ሊያቀርብበት ይችላል።

43.2 አንድ ጉዳይ የመስማት/የክርክር ሂደት ሳይኖር እንዲወሰን ለማድረግ የሚቻለው በጉባዔው ስምምነት ነው።

አንቀጽ 44- የመስማትሂደትለማከናወንዝግጅትስለማድረግ፣

44.1 ጉባዔው ጉዳዩን ለመሰማት ሂደት ዝግጁ ለማድረግ፣ የውሳኔ ወይም ውሳኔ ሐሳብ ረቂቅ ለማዘጋጀት፣ ለውሳኔ አሰጣጥ ጠቃሚ የሆኑ አጠቃላይ መረጃዎች ለማሰባብ ሲባል ከአባላቱ መካከል አንድ ሰው ይሰይማል። የጉባዔው ጽ/ቤት ባለሙያዎች ከተመደበው የጉባዔ አባል በመሆን ይሰራሉ።

44.2 በጉባዔው የተሰየመው አባል ጉዳዩን ለመሰማት ሂደት በሚያዘጋጅበት ወቅት አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች የማስቀረብ፣ ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግ የማዘዝ፣ ምርምሮች፣ የባለሙያ ግኝቶች እና አስተያየቶች ከንዑስ ጉባዔው ጋር በመመካከር እንዲቀርቡ የማዘዝ ሥልጣን ይኖሯል።

አንቀጽ 45- የመተባበርግዴታ

45.1 ማንኛውም አካል ጉባዔው እንዲቀርቡ የሚጠይቃቸው ሕጎች፣ ሰነዶችና ቅጂያቸው፣ የውሳኔ መዝገቦች፣ መረጃዎች፣ ጥናቶች፣ ግንኙቶች፣ የሙያ አስተያየቶች፣ ማብራርያዎች፣ መግለጫዎች ወዘተ የመስጠት ግዴታ አለበት።

45.2 ከላይ የተጠቀሱት መረጃዎች ለመስጠት የሚወጣው ወጪ መረጃውን በሚሰጠው የመንግሥት አካል የሚሸፈን ይሆናል። ነገር ግን መረጃው ከግለሰብ ወይም በመንግሥት በጀት ከማይተዳደር አካል የሚጠይቅ ሲሆን ወጪው በጉባዔው ጽ/ቤት የሚሸፈን ይሆናል።

45.3 በጉባዔው የተጠየቀው መረጃ አለመስጠት፣ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን ወይም በተጠየቀው ጊዜ ውስጥ አለመስጠት አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ያስጠይቃል።

አንቀጽ 46- መረጃዎችስለማሰራጨትናየመሰማትሂደትየሚካሄድበትስለማሳወቅ

46.1 የአቤቱታው ቅጂዎች፣ መልሶች፣ የሕገ መንግሥት ትርጉም የቀረበበት ሕግ እና ሌሎች ተያያዥ ሰነዶች ከመሰማት ሂደቱ አስር ቀን በፊት ለተከራካሪ ወገኖች እና ለጉባዔው አባላት ሊደርስ ይገባል።

46.2 የመሰማት ሂደቱ የሚደረግበት ቀን እና ሰዓት በጉባዔው ድህረ ገጽ፣ ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ቦታ በመለጠፍ እና ተደራሽነት ባላቸው የመገናኛ ብዙሃን ይገለጻል።

46.3 ጉዳዩ የተመራለት የጉባዔው አባል ከሰብሳቢው ጋር በመመካከር በመሰማት ሂደት ላይ የሚጋበዙ ወይም የሚጠሩ ሰዎች፣ የመሰማት ሂደቱ ስለሚመራበት አግባብ እና መረጃዎች ለሚመለከታቸው አካላት ስለሚደርስበት ሁኔታ አቅጣጫ ያስቀምጣሉ።

አንቀጽ 47- በመሰማትሂደትላይስለሚካፈሉአካላት

47.1 በአሰማም ሂደቱ የመካፈል መብት የሚኖራቸው ተከራካሪ ወገኖች፣ ተወካዮቻቸው፣ ምስክሮች፣ አስረጂዎችና አስተርጓሚዎች ይሆናሉ። ብዛታቸውም በጉባዔው የሚወሰን ይሆናል።

47.2 ጉባዔው በአሚከስ ኩሪነት አስተያየታቸውን ያቀረቡ አካላት በአሰማም ሂደቱ ላይ እንዲሳተፉ ሊጋብዝ ይችላል።

47.3 ተከራካሪ ወገኖች እኩል የመሰማት መብት አላቸው። ከዚህ በተጨማሪ በጉዳዩ ላይ ያላቸውን አቋም የመግለጽ፣ ጥያቄ የማቅረብ፣ ሌላኛው ወገን ያቀረበው አቤቱታ ወይም መልስ አስቀድሞ የማግኘት መብት አለው።

47.4 ተከራካሪ ወገኖቹ ወይም ተወካዮቻቸው በጉባዔው ጥሪ ከተደረገ በኋላ የመገኘት መብት አላቸው። የተከራካሪ ወገኖቹ ወይም ተወካዮቻቸው በመሰማት ሂደቱ አለመገኘት ጉባዔው ጉዳዩን ከማየት አያግድም። ሆኖም ግን ጉባዔው በቂና አሳማኝ መረጃ የቀረበለት እንደሆነ የመሰማት ሂደቱ ለሌላ ቀን ሊያስተላልፈው ይችላል።

አንቀጽ 48- የመሰማትሂደትበግልጽመድረክስለማድረግ

48.1 በሕገ መንግሥቱ ጉዳዩ በዝግ እንዲከናወን ከተደነገገው ጭ የመሰማት ሂደቱ በግልጽ መድረክ ይከናወናል።

48.2 የመሰማት ሂደቱን ለመቅዳት እና በቀጥታ በሬድዮ፣ በቴሌቪዥን፣ ወይም በሌላ መንገድ ለማስተላለፍ የጉባዔውን ፈቃድ በቅድሚያ ማግኘት አለበት።

48.3 ለጉባዔው እና ለተሳታፊዎች ደህንነት ሲባል በመሰማት ሂደቱ የሚሳተፉ ግለሰቦች ማንነታቸው የሚገልጽ መታወቂያ እንዲያሳዩ፣ የአካል እና የያዙት ቁሳቁስ ፍተሻ እንዲደረግበት በጉባዔው ሊታዘዝ ይችላል።

48.4 በመሰማት ሂደቱ የሚሳተፉ አካላት የጉባዔውን የአሠራር ስነ ስርዓት፣ መመሪያ፣ እና ለዕለቱ የወጣውን መርሃ ግብር እንዲሁም የሰብሳቢውን ትእዛዝ የማክበር ግዴታ አለባቸው።

48.5 ማንኛውም ግለሰብ ከላይ የተጠቀሱት በመሰማት ስነ ስርዓቶች የማያከብር ከሆነ ከተገቢ ማስጠንቀቅያ በጉባዔው ሰብሳቢ ትእዛዝ ከመድረኩ እንዲሰናበት ይደረጋል።

አንቀጽ 49- የመሰማትሂደትበዝግስለማድረግ

49.1 የመሰማት ሂደቱ በዝግ እንዲከናወን የሚደረገው በሕግ እንዲጠበቅ የተወሰነው ሚስጥር ለመጠበቅ፣ የሕብረተሰቡ ደሕንነትና ግብረ ገብነት ለማስጠበቅ አስፈላጊ ሲሆን ነው።

49.2 የዝግ መሰማት ሂደቱ የጉባዔው አባላት፣ የተከራካሪ ወገኖች ወይም ተመካዮቻቸው፣ የአሰማም ሂደቱ ለማሳለጥ የሚያስፈልጉ የጽ/ቤቱ ሰራተኞች በተገኙበት ይደረጋል።

49.3 በዝግ የመሰማት ሂደት ሲከናወን ሂደቱን መቅረጽ የተከለከለ ነው።

አንቀጽ 50- የመሰማትሂደቱንስለመክፈት

50.1 ሰብሳቢው የመሰማት ሂደቱ እንዲከናወን በተያዘው ቀጠሮ ምልአተ ጉባዔ መሟላቱን በማረጋገጥ የመሰማት ሂደቱ እንዲጀመር ያደርጋል።

50.2 ሰብሳቢው ተከረካሪ ወገኖቹ ወይም ተወካዮቻቸው ስለመገኘታቸው ያረጋግጣል።

50.3 ሰብሳቢው ተከራካሪ ወገኖቹ ወይም ወኪሎቻቸው እንዲሁም ሌሎች በጉባዔው የተጠሩ አካላት ወይም ሰዎች ያላቸው መብትና ግዴታ እንዲሁም የመስማት ሂደቱ አጭር ገለጻ ያደርጋል።

50.4 የመስማት ሂደቱ የሚጀምረው አመልካች/አመልካቾች በሚያቀርቡት ሐሳብ ነው። በመቀጠል ተጠሪ በአመልካች ሐሳብ ላይ በመንተራስ አስተያየቱን ያቀርባል።

50.5 የአመልካች እና የተጠሪ ሐሳብ ከተደመጠ በኋላ የአሚከስ ኩሪ ወይም የሙያ አስተያየት የሚያቀርቡ ካሉ ሃሳባቸውን እንዲሰጡ ይደርጋል።

50.6 ግራ ቀኙ አንዱ በሌላው ላይ እና በቀረቡ የሙያ አስተያየቶች ላይ በአጭሩ የበኩላቸውን ሐሳብ እንዲገልጹ ዕድል ይሰጣቸዋል።

50.7 የጉባዔ አባላት ለውሳኔ ወይም ለውሳኔ ሐሳብ አሰጣጥ አስፈላጊ ነው ብለው ያመኑትን የማጣሪያ ጥያቄዎች ለግራ ቀኙ እንዲሁም ለባለሞያዎች ሰብሳቢው በሚሰጠው ቅደም ተከተል መሰረት ያቀርባሉ።

አንቀጽ 51- ቀጠሮስለመቀየር

ጉባዔው የአሰማም ሂደቱ ከተከፈተ በኋላ በበቂና አሳማኝ ምክንያት ተከራካሪ ወገኖች ሲቀሩ፣ በአስገዳጅነት መገኘት ያለባቸው ምስክሮች ወይም አስረጂዎች ሳይገኙ ሲቀሩ እንዲሁም በጉዳዩ ላይ በቂ ዝግጅት ሳይደረግ በመቅረቱ የአሰማም ሂደቱን ቀጠሮ ሊቀይር ይችላል።

አንቀጽ 52- የተከራካሪወገኖችየማጠቃለያሐሳብ

52.1 የክርክሩ ሂደት ከመጠናቀቁ በፊት ጉባዔው ለተከራካሪዎች ወይም ተመካዮቻቸው የማጠቃለያ ሐሳብ እንዲሰጡ እድል ይሰጣል።

52.2 የማጠቃለያ ሐሳብ የሚቀርበው በመሰማት ሂደቱ ላይ የተነሱ ጉዳዮችን መሠረት በማድረግ ብቻ ነው።

አንቀጽ 53- የመስማትሂደቱንስለማጠናቀቅ

ጉባዔው በመሰማት ሂደቱ እንዲጣሩ የተያዙት ጭብጦች በበቂ ሁኔታ መጣራታቸውን በማረጋገጥ የአሰማም ሂደቱ መጠናቀቁን በመግለጽ መድረኩ ይዘጋል።

ክፍልአስር

የጉባዔውናየንዑስአጣሪጉባዔውስብሰባናውይይት

አንቀጽ 54- ምልዓተ ጉባዔ

54.2 ከጉባዔው አባላት ሁለት ሶስተኛው ከተገኙ ምልአተ ጉባዔ ይሆናል።

54.3 የጉባዔውን ስብስባ የጉባዔው ሰብሳቢ፣ ወይም ሰብሳቢው በሌሉ ጊዜ ምክትል ሰብሳቢ ይመሩታል።የቀረበውን ጉዳይ እነሱ የማያዩት በሆነ ጊዜ ሰብሳቢውና ምክትል ሰብሳቢዋ ድምጽ ሳይሰጡ ስብሰባውን ይመራሉ ያስተባብራሉ።

አንቀጽ 55.የጉባዔውውይይት

55.1 አንድ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ በጉባዔው ውይይት የሚደረግበት ጉዳዩ አስቀድሞ በንዑስ አጣሪ ጉባዔው ከታየ በኋላ ነው። ሆኖም ጉባዔው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው እንደጉዳዩ ዓይነት በቀጥታ ለጉባዔው ቀርቦ እንዲታይ ሊያደርግ ይችላል።

55.2 ንዑስ ጉባዔው በማጣራት ሂደት የሕገ መንግሥትትርጉም ያስፈልጋቸዋል ወይም አያስፈልጋቸውም የሚላቸውን በመለየት እንዲሁም እንደጉዳዩ ሁኔታ በምልዓተ ጉባዔ ውይይት ሊደረግባቸው ይገባል ያላቸውን ጉዳዮች ለጉባዔው ይልካል።

55.3 ጉባዔው በቀረቡለት አስተያየቶች ላይ ውይይት የሚያደርገው በጉዳዮቹ የአቀራረብ ቅደም ተከተል ላይ በመመስረት ነው። ሆኖም፡-

ሀ) አቤቱታው የአገርና የሕዝብን ጥቅም የሚመለከትና ለአጠቃላይ ሕገ መንግሥታዊ ስርአት መጎልበት ጠቀሜታ ያለው ከሆነ፣

ለ) ጉዳዩ የህጻናትን፣ የሴቶችን፣ በወንጀል ተከሰው በእስር ላይ ያሉ ሰዎችን፣ ከፍ/ቤት የተላኩ ጉዳዮችን፣የአካልና የአዕምሮ ጉዳተኞችን፣ የአረጋውያን መብት በቀጥታ የሚመለከት ከሆነ፣

ሐ) በጉዳዩ ላይ እግድ የተሰጠበት ከሆነ ወይም

መ) በሌላ አሳማኝ ምክንያት፣ በጉባዔው ሰብሳቢ ትዕዛዝ መሰረት ጉዳዮች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው በንዑስ ጉባዔው ተመርምረው ሊቀርቡይችላሉ።

55.4 ጉባዔው በአንድ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ላይ መወያየት ከጀመረ በኋላ የጉባዔ አባል ከተቀላቀለ የተቀላቀለው አባል በጉባዔው ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሐሳብ ላይ ድምጽ ሊሰጥ ይችላል።

አንቀጽ 56 - ስለንዑስአጣሪጉባዔስብሰባ

56.1 ሦስት የንዑስ አጣሪ ጉባዔው አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፣

56.2 የንዑስ አጣሪ ጉባዔው አባላት በያዟቸው ጉዳዮች ላይ በቋሚነት በመገናኘት የሚወያዩባቸውን የሳምንቱን ቀናት ይወስናሉ። ሆኖም አጣዳፊ ጉዳዮች ሲኖሩ በንዑስ አጣሪ ጉባዔው ሰብሳቢ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

አንቀጽ 57 - የንዑስአጣሪጉባዔውየውይይትሂደት

57.1 ንዑስ አጣሪ ጉባዔው የሕገመንግሥት ትርጉም ጥያቄ ወይም አቤቱታ መርምሮ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም ወይም ያስፈልገዋል ሲል በሙሉ ድምጽ የውሳኔ አስተያየት ለጉባዔ ሊያቀርብ ይችላል።

57.2 በንዑስ አንቀጽ 57.1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በቀረበው ጉዳይ ላይ የልዩነት ሐሳብ ካለ በአቤቱታው ተጨማሪ ምርመራ ተደርጎበት የአብላጫውና የልዩነት ሃሳቡ ለጉባዔውቀርቦ የሚወሰን ይሆናል፣

57.3 ንዑስ አጣሪ ጉባዔው አቤቱታውን በመመርመር ትርጉም አያስፈልገውም በማለት በሙሉ ድምፅ ውሳኔ የሰጠበት ጉዳይ ለጉባዔው ቀርቦ ከጸደቀ በኋላ መዝገቡ ይዘጋል፣

57.4 ማንኛውም የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ከፍ/ቤት የተላከ ከሆነ ንዑስ አጣሪ ጉዳዩን በመመርመር አስተያየት ተዘጋጅቶለት ለጉባዔው እንዲቀርብና እንዲወሰን ያደርጋል፣

57.5 ንዑስ አጣሪ ጉባዔው በአንድ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ላይ መወያየት ከጀመረ በኋላ የጉባዔ አባል ከተቀላቀለ አባሉ መሳተፍ ከመጀመሩ በፊት በተደረጉት ውይይቶችላይ በጉባዔው ሰብሳቢ በቂ ገለጻ ይደረግለታል፣

57.6 የንዑስ አጣሪ ጉባዔውሰብሳቢ የጉባዔው አባላት በቀረበው ጉዳይ ላይ ከተወያዩ በኋላ አባላቱ ድምጽ እንዲሰጡ በማድረግ በመጨረሻ ራሱ ድምጽ ይሰጣል፣

57.7 ንዑስ አጣሪ ጉባዔው ለጉባዔው የሚያቀርበው አስተያየት በጉዳዩ ውስጥ ባሉት በእያንዳንዱ ጭብጦች ላይ የሚያተኩር መሆን አለበት።

ክፍልአሥራአንድ

የጉባዔውውሳኔእናውሳኔየሐሳብ

አንቀጽ 58-ውሳኔእናየውሳኔሐሳብስለማሳለፍ

58.1 ጉባዔውበቀረበው ጉዳይ ላይ በቂ ማጣራት ካደረገበት እና አባላቱም በቂ ውይይት ተደርጎበታል ብለው ካመኑ በቀረበው ጉዳይ ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሐሳብ ያስተላልፋል።

58.2 የጉባዔው ውሳኔ እና ውሳኔ ሐሳብ የሚሰጠው የተገኙት አባላት በአቀማመጣቸው ቅደም ተከተል አንድ በአንድ በሚሰጡት ድምጽ ይሆናል። በየትኛውም ሁኔታ ሰብሳቢው ድምጽ የሚሰጠው በመጨረሻ ነው።

58.3 ጉባዔው ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሐሳብ አሳለፈ የሚባለው በውይይት ላይ ከተገኙት አባላት ውስጥ በአብላጫው አባል ሲደገፍ ነው።

58.4 በጉባዔው አባላት የተሰጠው ድምጽ እኩል ከሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሐሳብ ተቀባይነት እንዳገኘ ይቆጠራል።

58.5 በውይይት ላይ የተገኘ የጉባዔው አባል ድምጽ ያለመስጠት ወይም ድምጸ ተአቅቦ ማድረግ አይችልም።

58.6 በዚህ አግባብ የተዘጋጀው የውሳኔ ረቂቅ በቀጣዩ ቀነ ቀጠሮ ለጉባዔው ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ በአጣሪ ጉባዔው የተሰጠው የመጨረሻ ማስተካከያ ይዞ ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሐሳብ ሆኖ ይወጣል።

አንቀጽ 59- የልዩነትሐሳብ

59.1 ከአብላጫው የጉባዔ አባላት በሐሳብ የተለየ የጉባዔ አባል ወይም አባላት የልዩነት ሃሳቡ የውሳኔው አካል ይሆናል።

59.2 ማንኛውም የጉባዔ አባል በውጤት ደረጃ ከአብላጫው የጉባዔ አባላት ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሐሳብ ተስማምቶ ነገር ግን ለውሳኔው ወይም ውሳኔ ሃሳቡ መሠረት የሆነው ጭብጥ የተተነተነበት አግባብ ላይ ልዩነት ካለው የራሱንየማስማሚያ ሐሳብአዘጋጅቶ በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል።

59.3 የልዩነት ሀሳቡ ያለው የጉባዔ አባል የልዩነት ሃሳቡን በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ በጽሁፍ በማዘጋጀት ለጉባዔው ማቅረብ አለበት።

59.4 በጉባዔ አባላት የሚቀርቡ የልዩነት ሃሳቦች የጉባዔው ቃለ ጉባዔ እና የአብላጫ ድምጽ ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሐሳብ አካል ይሆናሉ።

አንቀጽ 60- የውሳኔወይምውሳኔሐሳብመነሻዎች

60.1 ጉባዔው ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሐሳብ የሚሰጠው በማጣራት ሂደት በተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ላይ በመመስረት ነው።

60.2 ጉባዔው በቀረበው የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ላይ ሳይወሰን አግባብነት ያለውን ጭብጥ በመለየት ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሐሳብ ሊሰጥ ይችላል።

አንቀጽ 61 - የውሳኔእናየውሳኔሐሳብይዘት

አጣሪ ጉባዔው የሚሰጠው ውሳኔ እና የውሳኔ ሐሳብ ቢያንስ የሚከተሉትን ዝርዝር ነጥቦች ሊይዝ ይገባል፦

ሀ. የጉባዔው ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሐሳብ የተሰጠበት ቀን እና ቦታ

ለ. ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሐሳብ ያሳለፉ የጉባዔ አባላት ስም

ሐ. በክርክሩ ተካፋይ የሆኑ ተከራካሪዎች ስም ዝርዝር እና አድራሻ

መ.የጉባዔው ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሐሳብ የጉዳዩን ፍሬ ሐሳብ፣ የተከራካሪዎችን አቤቱታ ይዘት በአጭሩ፣ የክርክሩ ጭብጥ፣ እንደዚሁም ጉባዔው ለምርመረው መሰረት ያደረገው የሕገ መንግሥት መንግሥት ድንጋጌና ውሳኔው ወይም የውሳኔው ሐሳብ ላይ የተደረሰበት ትንታኔና ድምዳሜ፣

ሠ.የአጣሪ ጉባዔው የሚሰጠው ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሐሳብ የሚፈጸም የውሳኔ ክፍል ይኖረዋል፤ ይህ ክፍል ውሳኔው የሚፈጸምበት አግባብ፣ የሚፈጽመውን አካል፣ የሚፈጸምበትን ጊዜ የሚያጠቃልል ይሆናል።

ረ. የአጣሪ ጉባዔው ትእዛዝ፣ ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሐሳብ አምስት ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በአባላቱ ሊፈረም ይገባል። ትዕዛዙ፣ ውሳኔው ወይም የውሳኔ ሀሳቡ እንደተሰጠ የሚቆጠረው በአባላቱ ፊርማ ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

ሰ. የጉባዔውን አባላት ፊርማ መያዝ አለበት።

አንቀጽ 62 - የውሳኔውተፈጻሚ ክፍል፣

62.1 የሕገ መንግሥት ትርጉም የተጠየቀበትን ውሳኔ በመሻር ተተኪ ውሳኔ መስጠት ወይም ማስረጃ ተጣርቶ እንዲወሰንወደ ፍርድ ቤት ለመመለስ የሚያስችልናይህንኑ የሚያመላክት መሆን አለበት።

62.2 የሕገ መንግሥት ትርጉም የተጠየቀበትን ሕግ በሙሉ ወይም በከፊል ኢ. ሕገ መንግታዊነቱን ለመወሰን የእርምት እርምጃ በሕግ አውጭው እንዲወሰድ ለማድረግ የሚያስችል መሆን አለበት።

62.3 ሕገ መንግታዊ የሆነውን ጉዳይ ለይቶ ማመልከት አለበት።

62.4 የሕገመንግሥት ትርጉም ጥያቄው መነሻ የፍርድ ቤት ውሳኔ ከሆነ ጉባዔው አቤቱታውን ካጣራ በኋላ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ካገኘው የሕገ ትርጉም የተጠየቀበት ውሳኔእንዲሻር፣ የሚጸና ውሳኔ ካለ እንዲጸና ወይም በአግባቡ ተጣርቶ የሚወሰንከሆነም ጉዳዩ ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ተመልሶ በአግባቡ እንዲወሰን ለማድረግ የሚያስችል የትዕዛዝ ክፍል መሆን አለበት።

62.5 በንዑስ አንቀጽ 62.4 የተደነገገው ቢኖርም ጉባዔው ጉዳዩ ወደ ፍ/ቤት ተመልሶ ከሚወሰን ይልቅ የተሻለ አማራጭ መኖሩ ስምምነት ላይ ከደረሰ የመሰለውን የአፈጻጸም አቅጣጫ ሊያሳይ ይችላል።

62.6 የአንድን ሕግ ሕገ መንግሥታዊነት የሚመለከት የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ተቀባይነት ካገኘ ጉባዔው ሕጉ ወይም የሕጉ ክፍል እንዲሰረዝ የውሳኔ ሐሳብ ለፌደሬሽን ምክር ቤት ሊያቀርብ ይችላል።

62.7 በንዑስ አንቀጽ 62.6 ላይ የተደነገገው ቢኖርም የሕጉ ወይም የሕጉ ክፍል መሰረዝ ከፍ ያለ ቀውስ የሚያስከትል ከሆነ ሕጉ ወይም የሕጉ ክፍል እስከሚሻሻል እስከ ስድስት ወር ተፈጻሚነት እንዲኖረው ሊደረግ ይችላል።

አንቀጽ 63- ውሳኔስለማስፈጸም

63.1 በጉባዔው የተሰጠው የውሳኔ ሐሳብ በፌ/ም/ቤት ተቀባይነት ካገኘ በኋላ የሚፈጸመው በጉዳዩ ላይ የአካባቢ ሥልጣን ባለው የፌደራል ወይም የክልል ፍ/ቤት ነው።

63.2 የተሰጠውን ውሳኔ አለማስፈጸም፣ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ሙሉ በሙሉ አለማስፈጸም ወይም በአፈጻጸም ላይ መሰናክል መፍጠር በሕግ ተጠያቂነት ያስከትላል።

አንቀጽ 64 - ውሳኔስለማሳወቅ፣

64.1 ጉባዔው ውሳኔ በሰጠበት ዕለት ወዲያውኑ በጉባዔው ሬጅስትራር በኩል ውሳኔውን ለአቤቱታ አቅራቢ ያሳውቃል።

64.2 ጉባዔው የሰጠው ውሳኔ ግልባጭ ለተከራካሪዎች ወይም ሌሎች ውሳኔውየሚመለከታቸው ባለጉዳዮች በጠየቁ ጊዜ ይሰጣቸዋል።

አንቀጽ 65- የጉባዔውንውሳኔወይምየውሳኔሐሳብስለማረም፣

ጉባዔው በውሳኔው ወይም በውሳኔ ሃሳቡ ላይ የተፈጠሩ የስም ወይም የቁጥር ስሕተት፣ የፊደል ወይም መሰረታዊ የሆነ የሐሳብ ግድፈት ማስተካከል ይችላል።

አንቀጽ 66 - ስለይግባኝ

ጉባዔው መርምሮ የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልጋቸውም በማለትውሳኔ በሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ ለፌዴሬሽን ም/ቤት ይግባኝ ሊጠይቅባቸው ይችላል።

አንቀጽ 67- የውሳኔሐሳብስለመላክ፣

67.1 ጉባዔው የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልጋቸዋል በማለት የውሳኔ ሐሳብ የሰጠባቸው ጉዳዮች በጉባዔው ሰብሳቢ ፊርማከሌሎች አባሪ ሰነዶች ጋር ተያይዘው ለፌዴሬሽን ም/ቤት ይላካሉ።

67.2 ጉባዔው ለምክር ቤቱ የላከው የውሳኔ ሐሳብ በፌዴሬሽን ምክር ቤትወይም በሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ውይይት በሚደረግበት ጊዜ አስረጂ ሆኖ ሊቅርብ ይችላል።

67.3 ምክር ቤቱ በቀረበለት ጉዳይ ላይ ውይይት ካደረገበት በኋላ ተጨማሪ ምርመራ ያስፈልገዋል ብሎ ሲያምን የሚጣራውን ነጥብ በመለየት መልሶ ለጉባዔው ሊልከው ይችላል።

ክፍልአሥራሁለት

ልዩልዩ

አንቀጽ 68 - የእግድጥያቄአወሳሰን

68.1 ጉባዔው በቀረቡለት የትርጉም ጥያቄዎች ወይም አቤቱታ ላይምርመራ አድርጐ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ወይም የውሳኔ ሐሳብ እስኪያቀርብ ድረስ ዕግድ የተጠየቀባቸውን ጉዳዮች የንዑስ አጣሪ ጉባዔው ቅድሚያ ሰጥቶ እንዲያይ ሊያደርግ ይችላል።

68.2 አንድ የእግድ ጥያቄ አቤቱታ ቢያንስ የሚከተሉትን ምክንያቶች ሊያሳይ ይገባል፦

ሀ. የእግድ ጠያቂው ወገን በእግድ አቤቱታው ውስጥ በጉዳዩ ፍሬ ነገር እና በተቀባይነቱ ላይ ጭብጥ ያለው ስለመሆኑ፣ እና

ለ. እግዱ ባይፈቀድ ሊመለስ የማይችል ጉዳት የሚደርስ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አለበት፣

ሐ. እንደአግባብነቱ እርምጃው የሕዝብ ጥቅም ውስጥ የሚካተት መሆኑን ማሳየት አለበት።

68.3 የንዑስ አጣሪ ጉባዔው የእግድ ጥያቄውን ሲመረምር አቤቱታውን ካቀረበው ወገን ወይም ጉዳዩን ለማጣራት ተገቢ ከሆነ አካል ተጨማሪ ፍሬ ነገሮች፣ ዶክመንቶች ወይም መረጃዎች እንዲቀርቡ ሊጠይቅ ይችላል።

እንደዚሁም ተቃራኒው ወገን መልሱን ወይም ተጨማሪ ፍሬ ነገሮች፣ ዶክመንቶች ወይም መረጃዎች እንዲያቀርብ የንዑስ አጣሪ ጉባዔው ሊያዝ ይችላል፣

68.4 የንዑስ አጣሪ ጉባዔው በእግድ ጥያቄው ላይ ከተወያየ በኋላበጉባዔው ሰብሰቢ እግዱ እንዲሰጥሐሳብ ሊያቀርብ ይችላል። የአጣሪ ጉባዔው ሐሳብ የፍ/ቤት ትእዛዙ ከሚፈጸምበት በፊት በቃለ ጉባዔ ተረጋግጦ በጉባዔው ሰብሳቢ ፊርማ ትእዛዙን ለሚያስፈጽመው አካል ወይም ለሚመለከተው አካል ይላካል።

68.5 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አራት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የጉባዔው ሰብሳቢ ንዑስ ጉባዔው ለመሰብሰብ በማይችልበት እና አጣዳፊ በሆኑ የእግድ ጥያቄዎች ላይ መርምሮ የእግድ ትእዛዝ የመስጠት ሥልጣን አለው።

68.6 በጉባዔው በተሰጠ የዕግድ ትዕዛዝ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን እግዱ እንዲነሳለት ጥያቄ ማቅረብ ይችላል። የጥያቄው ይዘትና ሥነ ሥርዓቱ በዚሁ አንቀጽ ስር ለእግድ ጥያቄ አቤቱታ በተቀመጡት አግባብ ይሆናል።

አንቀጽ 69- የጉዳዮችንሚስጥራዊነትስለመጠበቅ

69.1 በጉባዔው በመጣራት ላይ ያሉ ጉዳዮች ሚስጥራዊነታቸው የተጠበቀ ነው።

69.2 የጉባዔው አባላት፣ ባለሞያዎችና ጉባዔው ፍቃድ የሰጣቸው አካላት በሥራቸው ምክንያት ስለ አንድ ጉዳይ በእጃቸው የሚገኝን መረጃ በሚስጥር መጠበቅ አለባቸው።

69.3 ተከራካሪ ወገኖች የሚከራከሩበትን ጉዳይ በተመለከተ በአጣሪ ጉባዔው ሚስጥራዊ እንዲሆን ካልተወሰነ በቀር ፋይሉን እና ሌሎች ዶክመንቶችን የማየትና ኮፒ የማግኘት መብት ይኖራቸዋል። ለኮፒዎቹ አስተዳደራዊ ክፍያዎችን በተመለከተ በሚወጣው መመሪያ መሰረት ጽ/ቤቱ ሊያስከፍል ይችላል።

አንቀጽ 70- የጉዳዮችፋይልአያያዝ

የአንድን ጉዳይ የማጣራት ሂደት የሚመለከቱ ሰነዶች በጉዳዩ ፋይል ውስጥ ተመዝግበው መያዝ አለባቸው። ሆኖም የዝግጅት ሰነዶች፣ የድምጽ አሰጣጥ ሂደትን የሚያሳይ ቃለ ጉባዔና ሌሎች ተያያዥ ሰነዶች በጉዳዩ ፋይል ውስጥ አይቀመጡም።

አንቀጽ 71- የመወከልመብት

ተከራካሪዎች ወይም በክርክሩ ጥቅማቸው የሚነካና ወደ ጉዳዩ እንዲገቡ የተፈቀደላቸው አካላት በጉባዔው ሲቀርቡ የመወከል መብት አላቸው።

አንቀጽ 72- ስለጉባዔውየሥራቋንቋ

72.1 ለጉባዔው የሚቀርቡ አቤቱታዎችና አስተያየቶችየሚቀርቡት በፌደራል መንግሥት የሥራ ቋንቋ ነው፤ የሥራ ቋንቋውን የማይችል አስተያየት ሰጪ አስተያየቱን በሚችለው ቋንቋ እንዲያቀርብ ይደረጋል።

72.2 አስተያየታቸውን በሌላ ቋንቋ ለሚያቀርቡ ተሳታፊዎች የጉባዔው ጽ/ቤት የቋንቋ አስተርጓሚ ይመድባል።

72.3 አስተያየት ሰጪዎች መስማት የተሳናቸው በሆኑ ጊዜም ተገቢው አስተርጓሚ ይቀርብላቸዋል።

72.4 ጉባዔውም ለአስተርጓሚነት የቀረበውን ግለሰብ ቃለ መሃላ በማስፈፀም የትርጉም አገልግሎት እንዲሰጥ ያደርጋል።

አንቀጽ 73- የጉባዔአባላት፣የጠበቆችናየተሳታፊዎችየአለባበስደንብ

73.1 የጉባዔው አባላት በጉዳዮች አሰማም መድረክ ላይ በጉባዔው የተወሰነውን የአለባበስ ርዓት ይከተላሉ። ዝርዝሩ ጉባዔው በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

73.2 በመድረኩ ተከራካሪዎችየሚወክሉ ጠበቆች በመደበኛ ፍ/ቤት ላይ ጠበቆች እንዲለብሱ የተወሰነውን ካባ ለብሰው መቅረብ አለባቸው።

73.3 በመድረኩ ላይ ሙያዊ አስተያየት እንዲያቀርቡ የተፈቀደላቸው ሰዎች የጉባዔውን ክብር የሚመጥን አለባበስ መልበስ አለባቸው።

አንቀጽ 74- ከሚዲያዎችጋርየሚደረግግንኙነት

74.1 ጉባዔው እውቅናና ተደራሽነት ያላቸውን የህትመት እና የመገናኛ ብዙሃን ድርጅቶችን በጉዳዮች አሰማምና አስተያየት በሚቀርብበት መድረክ ላይ እንዲገኙ ጥሪ ሊያደርግ ይችላል።

74.2 የጉባዔው ጽ/ቤት ጥሪውን በተቋሙ ማስታወቂያ ቦርድ፣ ኦፊሴላዊ ዌብሳይት የሚያደርግ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱም በሌሎች የመገናኛ ብዙኃን አማካኝነት ሊያስተላለፍ ይችላል።

74.3 የጉባዔው ሰብሳቢ ወይም የሚመድበው የጉባዔው አባል ወይም የጉባዔው ፅ/ቤት ኃላፊ በመድረኩ ላይ ከሚሳተፉ የሚዲያ ተቋማት ተወካዮች ጋር ግንኙነት የሚፈጥር ሲሆን የሚከተሉት ተግባሮች ይኖሩታል፦

ሀ. የጉባዔውን ሥራ በተመለከተ ለሚዲያዎች ጋዜጣዊ መግለጫ ይሰጣል፤

ለ. በጉባዔው የተያዙ አጀንዳዎችን ያሳውቃል፤

ሐ. የጉባዔውን አጠቃላይ አሠራር በተመለከተ ለሚመለከታቸው አካላት መረጃ ይሰጣል።

አንቀጽ 75- የመገናኛብዙሃንየመረጃአጠቃቀም

75.1 የክርክሩ ወይም የሙያ አስተያየቱ አሰማም በከፊል ወይም በሙሉ ዝግ ሆኖ እንዲፈፀም አስቀድሞ በጉባዔ ካልተወሰነ በቀር መድረኩ ለመገናኛ ብዙሃን ክፍት ይሆናል።

75.2 አስቀድሞ በልዩ ሁኔታ በጉባዔው ካልተከለከለ ወይም የመሰማት ሂደቱን የሚያደናቅፍና የሚያስተጓጉል ሆኖ ካልተገኘ በቀር መገናኛ ብዙሃን በጉዳዮች የመሰማት ሂደት ወቅት ፎቶ ማንሳትም ሆነ ቪዲዮ መቅረፅ አይከለከሉም።

75.3 መገናኛ ብዙሃን በጉባዔው አሠራር ላይ ተመስርተው የሚሰሩት ዘገባ ፍትሃዊ፣ ገለልተኛና ሚዛናዊ ሊሆን ይገባል።

75.4 በጉባዔው አሠራር ወቅት ካገኙት መረጃ ጋር በተያያዘ የጉባዔውን፣ የጉባዔውን አባላት፣ የባለጉዳዮችን ወይም የሙያ አስተያየት ሰጪዎችን መልካም ስምና ክብር በሚጎዳ መልኩ ዘገባ ሰርተው ሲገኙ የጉባዔው ፅ/ቤት ይህን እንዲያርሙ ይጠይቃል።

75.5 መገናኛ ብዙሃን ከጉባዔው ሥራ ጋር ተያይዞ ስለሚያገኙት መረጃ አጠቃቀምና ተጠያቂነት ሁኔታ አግባብነት ያለው የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

አንቀጽ 76- የመድረኩሥነሥርዓትአከባበር፣

76.1 የመድረኩን ደህንነትና ጸጥታ የሚያስከብሩ አካላት ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ጋር በመነጋገር ይመደባል።

76.2 በአስተያየት አሰማም መድረክ ላይ የሚገኙ ተሳታፊዎች የጉባዔውን አሠራርና የመድረኩን ሥነ ሥርአት የማክበር ግዴታ ያለባቸው ሲሆን የጉባዔውን ሥራ ከሚያውክና ዓላማውን ከሚያደናቅፍ ድርጊት መቆጠብ ይኖርባቸዋል።

76.3 በመድረኩ ተሳታፊ ሆኖ የጉባዔውን ሥራ የሚያውክ ወይም የጉባዔው አባላትና ሌሎች ተሳታፊዎች ላይ ያልተገባ ባህሪ የሚያሳይ ከሆነ ከአዳራሹ ጭ እንዲወጣ ሊያደርግ ይችላል። በተጨማሪም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በመደበኛ የወንጀል ህግ መሰረት ተጠያቂ ይደረጋል።

76.4 ድርጊቱን የፈፀመው ተከራካሪ ወገን በሆነ ጊዜ ተከራካሪው ከአዳራሹ እንዲወጣ ሊያደርግ ይችላል።

አንቀጽ 77- ለሙያአስተያየትአቅራቢዎችየሚፈፀምክፍያ

77.1 የሙያ አስተያየት አቅራቢዎች ለሚያቅረቡት የሙያ አስተያየት ጉባዔው የተለየ ክፍያ አይፈጽምም።

77.2 ጉባዔው የሙያ አስተያየት ከሚሰማበት ከተማ ጭ ለሚመጡ ባለሙዎች አስፈላጊውን የትራንስፖርት፣ የመኝታ፣ የምግብ እና የውሎ አባል ወጪ ይሸፍናል።

አንቀጽ 78- የመስማትሂደትመረጃአያያዝ

78.1 በመስማት ሂደቶች ወቅት የነበሩ አጠቃላይ ኩነቶችን መረጃ ለመያዝ በሚያመች መልኩ ጽ/ቤቱ ቃለ ጉባዔ ይያዛል።

78.2 በተጨማሪም በሂደቱ የቀረቡ የግራ ቀኙ ክርክሮች፣ የተሰጡ የባለሙያ አስተያየቶች፣ የጉባዔ አባላት ጥያቄዎችና ምላሾች በሰነድና በድምፅ ተቀድተው በጉባዔው ፅ/ቤት እንዲቀመጡ ይደረጋል።

78.3 የሕገ መንግሥት ትርጉም ምርመራ የተደረገባቸውና የተጠናቀቁ መዝገቦች ላይ የተገኙ መረጃዎች በክርክሩ በአመልካችነት ወይም በተጠሪነት የተሳተፉ አካላት ሲጠይቁ የድምፅ ቅጂውን የማዳመጥ ወይም በራሳቸው ወጪ (ኮፒ ተደርጎ ሊሰጣቸው ይችላል። ሆኖም በዚህ መልኩ የወሰዱትን የድምፅ ቅጂ ለሌላ ዓላማ ወይም ጥቅም ማዋል አይፈቀድም።

አንቀጽ 79 - ስለ ይርጋ

79.1 በፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የቀረበ የሕገ መንግሥት ትርጉም አቤቱታ ተቀባይነት የሚያገኘው የመጨረሻ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ 3 ወርጊዜ ውስጥ ሲቀርብ ነው።

79.2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 79.1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አቤቱታው አለመቅረቡ ሲረጋገጥ በጉባዔው ተቀባይነት ሊያገኝ ይችላል።

79.3 ማንኛውም የመንግሥት አካል ወይም የባለሥልጣን ውሳኔ ላይ የሚቀርብ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ውሳኔው ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር በ 3 ወር ይርጋ ይታገዳል።

79.4 የሕግ ሕገ መንግሥታዊነትን በሚመለከት የሚነሳ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ በይርጋ አይታገድም።

79.5 ማንኛውም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ድርጊት ላይ የሚቀርብ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ሊቀርብ የሚችለው ድርጊቱ መፈፀሙ እስከቀጠለ ድረስ ነው።

አንቀጽ 80 - ቃለመሀላ

80.1 ለጉባዔ አባልነት በኢፌዴሪ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት የሚሾሙ አባላት በሾማቸው አካል ፊት ቀርበው ቃለ መሐላ ይፈጽማሉ።

80.2 ቃለ መሃላ አፈፃፀም ስነ ሥርዓትን በተመለከተ የጉባዔው እና የፕሬዝዳንት ጽ/ቤቶች በጋራ የሚያስተባብሩ ሲሆን ቃለ መሃላውም በጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት የሚፈፀም ይሆናል።

80.3 የቃለ መሃላ አፈፃፀም ስነ ሥርዓት ለጉባዔ አባላት በሚመጥን ደረጃ የሚከናወን ሲሆን የፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባዔ፣ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ፣ የሪፐብሊኩ ፕሬዝዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ የጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት እና የክልል ርእሰ መስተዳደሮች በሚገኙበት ይሆናል።

80.4 በጉባዔው አባላት የሚፈጸመው ቃለ መሃላ የሕገ መንግሥቱን የበላይነት ለማክበርና ለማስከበር በቅንነትና በታማኝነት ለማገልገል ቁርጠኛ መሆኑን የሚያንጸባርቅ ይሆናል።

አንቀጽ 81- የጉባዔአባላትሽኝት

81.1 የራ ዘመናቸውን ያጠናቀቁ የጉባዔ አባላት በኢፌዴሪ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት ሽኝት ይደረግላቸዋል።

81.2 የሽኝት ፕሮግራሙም ለጉባዔ አባላት በሚመጥን ደረጃ በጉባዔው እና በፕሬዝዳንት ጽ/ቤቶች በጋራ የሚከናወን ሲሆን የፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባዔ፣ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ፣ የሪፐብሊኩ ፕሬዝዳንት እና ጠቅላይ ሚኒስትር እና የጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት በሚገኙበት ይሆናል።

አንቀጽ 82- መመሪያ የማውጣት ሥልጣን፣

የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ለዚህ የአሠራር ስነ ሥርዓት ደንብ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

አንቀጽ 83 - ስለሌሎችሕጎችተፈጻሚነት

83.1 በዚህ የአሠራር ስነ ሥርዓት ደንብ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ አግባብነት ያላቸው የፍትሐብሄር ሥነ ሥርአት ሕግድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

83.2 ይህን የአሠራር ስነ ሥርዓት ደንብ የሚቃረን ማናቸውምሕግ ወይም ልማዳዊ አሠራር ተፈፃሚነት አይኖረውም።

አንቀጽ 84- የአሠራርሥነሥርዓት ደንቡንስለማሻሻል

84.1 ማንኛውም የጉባዔው አባል ይህ የአሠራር ስነ ሥርዓትደንብ እንዲሻሻል ሐሳብ ሊያቀርብ ይችላል።

84.2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 83.1 የተመለከተው የማሻሻያ ሐሳብ መቅረብ ያለበት በጽሁፍ ሆኖ የሚሻሻለውን የአሠራር ስነ ሥርዓትደንብ ክፍል ከነምክንያቱ እና በተተኪነት የቀረበውን የማሻሻያ ሐሳብ የያዘ መሆን አለበት።

84.3 የቀረበው የማሻሻያ ሐሳብ በጉባዔው አብላጫ ድምፅ ተቀባይነት ካገኘ ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት ቀርቦ ሲጸድቅ ተግባር ላይ ይውላል።

አንቀጽ 85- የአሠራር ስነ ሥርዓት ደንቡ ተፈጻሚነት

ይህ የአሠራር ስነ ሥርዓትደንብ በፌዴሬሽን ም/ቤት ከጸደቀበት ከዛሬ ሰኔ 25 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

አቶ አገኘሁ ተሻገር ገሰሰ

የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባዔ